የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ
አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)

Amara Survival For Ethiopia's
Unity Organization (ASEUO)

06/6/2020

የትግላችን ግብ ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤት ማድረግ ነው!

## ሕገ-መንግሥቱን ከሚሻሻል እንደገና መጻፍ ተቀባይነቱን አሳድጎ ሥራውን ያቀለዋል !

ዓለም አቀፉ የሣናባ ቆልፍ (ኮቪድ-19) የተሰኘው ተላላፊ በሽታ በጋረጠው ችግር ሳቢያ፣ ላለፉት 28 ዓመታት፣ ያልተመረጡትን ተመረጡ እያለ «ሲያስመርጥ» የነበረው «የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ» 6ኛውን ዙር ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ወቅቱን ጠብቆ ማካሄድ እንዳይቻል እንዳደረገው አሳውቋል። እንደዚህ ያሉ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ሲከሰቱ በምን መንገድ ችግሮቹን መወጣት እንደሚቻል፣ ሕገ-መንግሥቱ የደነገገው ባለመኖሩ፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦችን ሲሰነዝሩ እያስተዋልን ነው። በርካታዎቹ ከመጀመሪያውም ሕዝቡ የታገለው እና እየታገለም ያለው የአገሪቱና የሕዝቡ የችግር ቋጠሮው ሕገ-መንግሥቱ ስለሆነ፤ እርሱ መለወጥና በአዲስ ሕዝቡ የኔ በሚለውና የሕዝቡን ፍላጎት ያካተተ ሕገ-መንግሥት ይተካ። ለዚህም የሽግግር ሥርዓት ይኑረን የሚለው የብዙዎቹ ድርጅቶች ጥያቄ መሆኑ ይታወሳል። የዚህ ሀሳብ አራማጆች አክለውም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ለሽግግር መንግሥት ምሥረታ ፈቃደኛ ካልሆነ ደግሞ፣ የምርጫ ጊዜው መራዘም አለበት፣ የሚል አቋም ይዘው በኅብረትም በተናጠልም ሲያሰሙ መቆየታቸው አይዘነጋም።

በሌላ በኩል ሕገ-መንግሥቱን ያረቀቁና ያፀደቁ፣ በዚህም ተጠቃሚ የሆኑ፣ በኢትዮጵያ አንድነትና በዐማራ ላይ የከረረ ጥላቻ ያላቸው የነገድ ድርጅቶች ፣ «ሕገ-መንግሥቱ ችግር የለበትም። ችግሩ አፈጻጸሙ ዲሞክራሲያዊ አለመሆኑ ነው። ስለሆነም ሕገ-መንግሥቱ መለወጥ ቀርቶ ከነአካቴውም መነካት የለበትም» የሚለውን ሀሳብ አክረው የያዙ ድርጅቶች እንዳሉ ግልጽ ነው።

በአንፃሩ፣«ብልጽግና ፓርቲ»፣ በመሪው አማካኝነት ሕገ-መንግሥቱ ሊሻሻል እንደሚችል በተደጋጋሚ ቢገልጹም፣ በተግባር ግን ያሳዩት እርምጃ ካለመኖሩም በላይ፣ አገሪቱ የገጠሟትን ችግሮች ሁሉ በሕገ-መንግሥቱ ማዕቀፍ ይፈታሉ። ከሕገመንግሥቱ ውጭ ያሉትን አማራጮች አንቀበልም፤ የሽግግር መንግሥቱን ጥያቄ «እኔ  አሻግራችኋለሁ !» ከማለት ዘለው፣ «የሽግግር መንግሥት የሚጠይቁ በአቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ የሚፈልጉ ናቸው። የሽግግር መንግሥት የብጥብጥ መንግሥት ነው።» በማለት ጥያቄዎቹን አራሙቻ ጥለውባቸዋል።  ጥያቄ አቅራቢዎቹንም የተለያዩ ስሞች እየሰጡ አንገት ለማስደፋት ሲጥሩ እያስተዋልን ነው። በዚህ አቋማቸው ጸንተው ለትክክለኛ ምርጫና ለሂደቱ ታማኒነት ምርጫውን የሚገዛው ሕገመንግሥት ሳይሻሻል ወይም ሳይለውጥ ቀኑን ጠብቆ ምርጫው መካሄድ አለበት የሚል አቋም ይዘው እንደነበርም ይታወቃል።

ሆኖም፣ ከማናችንም ዕውቅና ውጪ የሆነ፣ ሕገ-መንግሥቱም እንዲህ ያለ ነገር ቢከሰት ምን መደረግ እንዳለበት ፍንጪ ባልሰጠበት ሁኔታ፣ «የሣንባ ቆልፍ» ዓለም አቀፍ በሽታ መከሰት፤ ለምርጫው ቋምጠው የነበሩትን ኃይሎች ፍላጎት ተፃራሪ የሆነ ክስተትን አስከተለ። ይህ ችግር በማንም ፍለጎት የተከሰተ አይሁን እንጂ፣ ለእንደዚህ ያሉ ችግሮች መውጫ በር ያላዘጋጀው ሕገ-መንግሥቱ በመሆኑና፣ ችግሩ በግልጽ መከሰቱና ሕገ-መንግሥቱም መልስ አለመኖሩ በራሱ፣ ሕገ-መንግሥቱ መሻሻል ወይም መቀየር እንዳለበት አመላካች ሁኔታን መፍጠሩ ገሐድ ነው።

ይህን ችግር ማለፍ ያለብን በማን አለብኝነት፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ፣ በዚህ ጉዳይ ባለቤቱ እኔ ወይም እኛ ነን፣ የሚሉት ባለፉት 50 እና 60 ዓመታት ተጉዘንባቸው መፍትሔ ሳይሆን፣ ችግሮችን በደረደሩ ሀሳቦችና አመለካከቶች መሆን የለበትም። እንደዚህ ያሉ አገርና ሕዝብን ያማከሉ ጉዳዮች ሲገጥሙን፣የሚመለከታቸው ወገኖች በተናጠልና በቡድን ሀሳባቸውን እና አመለካከታቸውን ያላንዳች ተጽዕኖ የማቅረብና በዲሞክራሲያዊ አግባብ ውሳኔ ላይ እየተደረሰ፣ **ሁሉም የጠየቀውን ሳይሆን፣ የሚገባውን እያገኘ** ፣ የሩቅ ጊዜ ግባችን ለሆነው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሥፈን ጉልህ አስተዋጽዖ ሊያበረክት በሚችልበት አቅጣጫ መጓዝ እንዳለብን ላፍታም ልንዘነጋው አይገባም።

ዲሞክራሲ ስንል፣ሁሉም እኔ ያልኩት ይሁን ማለት አይደለም። ሀሳብ ያቀረበ ሁሉ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለትም አይደለም። የጠየቀውን ሁሉ የሚያገኝበት ሳይሆን፣ የሚገባውን የሚያገኝበት ነው። ለዚህም መወያየትን፣ መከራከርን፣ መተማመንና መቻቻልን ይጠይቃል። ዲሞክራሲ፣ ያሉ ሀሳቦች ዕኩል የመደመጥ፣ ዕኩል የመሳተፍ እና በአብላጫ ድምፅ የመገዛት ሥርዓት ነው። ማንም እንደሚገነዘበው፣በዲሞክራሲ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት የአብዛኛውን

ሕዝብ ፍላጎት ገዥ የሆኑ ሀሳቦች ባለቤት መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ሀሳቦቹን ሕዝቡ እንዲገዛቸው እና የራሱ እንዲያደርጋቸው የሁለንተናዊ ዐቅም ባለቤት መሆንን ይጠይቃል።

በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ፣ ይህ ሁለንተናዊ ዐቅም፣ ወደድንም ጠላንም የመንግሥትን ሥልጣን በያዘው ኃይል እጅ ነው። የገንዘብ፣ የቁሣቁስ እና የሰው ኃይል ዐቅሙ ብቻ ሳይሆን፣ ኃይልን የመጠቀም መብትና ሥልጣን ያለው አካል ነው። የፈለገውን በፈለገው ጊዜ የማድረግ መብትም «ሥልጣንም ባለቤት» መሆኑን ላንዳፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። «ባለሥልጣን ለመነ፣ አዘዘ » ነውና አባሎቹን ብቻ ሳይሆን፣ ዜጎችን በልመና ስም አስገድዶ ፍላጎቱን የማስፈጸም አጋጣሚው ወይም ዕድሉ በእጁ ነው። ተቃዋሚዎች ይህን የማድረግ አጋጣሚውም ሆነ ዕድሉ የላቸውም። ይህም «ብልጥ ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል» ነውና፣ አሁን አገራችን ለገጠሟት ችግሮች መፍትሔው የመንግሥትን አስገዳጅ ተቋሞች በእጁ ካደረገው ኃይል ጋር እልክ መግባት ሳይሆን፣ ነገ ሕዝባችን በተጨባጭ ባደረግነውና በምናደርገው እንቅስቃሴ ገምቶ፣ የኔ እንዲለንና ድምፁን እንዲሰጠን በሚያስችል ሁኔታ የገጠሙትን ችግሮች ለመፍታት እንጂ፣ ከችግሮቹ ላይ ችግሮች የሚደራርቡ ወደ ጎንም ሆነ ወዳላይና ወደታች ሽኩቻ ከመግባት መቆጠብ ብልኅነት ብቻ ሳይሆን አዋቂነትም ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ ተነስተን፣ ትናንት ምርጫው ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው መንገድ መሠረት መደረግ አለበት ያለን፣ የብልጽግና ፓርቲ አመራር፣ ዛሬ በተፈጠረው ዓለም አቀፍ የሕዝብ ጤና ችግር ሳቢያ፣ የምርጫውን ጊዜ ለማራዘም መገደዱን እያየን ነው። ይህ ችግር የሁሉም ከመሆኑም በላይ፣ ድሮም አንዳንዶቻችን ምርጫው መራዘም አለበት የሚል አቋም ለነበረን፣ ሁኔታው «ገንፎ ሲያምርበት ተንከባሎ ከቅቤ ማሰሮ ይገባል» የሚሉት ዓይነት ሁኔታ የፈጠረልን በመሆኑ፣ እንዲራዘም የፈለግንበትን ምክንያቶች ለማከናወን እንድንጠቀምበትና በሁለንተናዊ ዐቅማችን ተጠናክረን እንድንወጣ ዕድል ሰጥቶናል።

የምርጫው መራዘም በማንም ፍላጎት ተጽዕኖ ሳይሆን፣ በዓለም ላይ በተከሰተ የሕዝብ የጤና ችግር በመሆኑ፣ በምርጫው ጊዜ መራዘም የተከፋ ወይም ለምን ብሎ የጠየቀ አካል ካለ ትሕነግ/ሕወሓት ብቻ ነው። ጥያቄ ያለው እንዴት ምርጫው ይራዘም? እስከመቼ ይራዘም? ከተራዘመስ በሕገ-መንግሥቱ መሠረት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 3 «የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጠው ለአምስት ዓመታት ነው፤ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል።» የሚለው የምክር ቤቱን አባሎችና በዚሁም ምክር ቤት ተመርጦ ሥልጣን የጨበጠውን ኢሕአዴግ/ብልጽግናን የሥልጣን ዘመን

ማለቅ የሚያረጋግጥ ስለሆነ፣ከመስከረም 30/2013 በኋላ የመንግሥት ሥልጣን በማን እጅ ይሁን? የሚሉት ናቸው።

ለነዚህ ጥያቄዎች ሕገ-መንግሥቱ መልስ የለውም። እንደዚህ ያሉ ያልተጠበቁ ጉዳዮች ቢከሰቱ በምን መልክ መስተናገድ እንዳለበት ሕገ-መንግሥቱ የሚሰጠው ፍንጭ የለም። ፍንጮች አሉ ከተባለም የሕግ ሙያተኞች ከሌሎች አገሮች ልምድ በመቅሰምና እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሲከሰቱ እንዴት መፍታት እንደሚቻል የሚያቀርቧቸው ምክረ ሀሳቦች ናቸው። እነዚህን ምክረ ሀሳቦች መቀበል ፣ማዳበር፣ ማስፋፋት ደግሞ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ወደፊትም ከሕዝባችን ሁለንተናዊ ዕድገት ጋር ተያያዞ ሊከሰቱ ለሚችሉ ሕገ-መንግስታዊ ጥያቄዎች የልምድ መሠረት ሊጥል ስለሚችል ፣አጋጣሚውን በአፍራሽ መልኩ ከማዬት በበጎ ጎኑ ተመልክተን የምንችለውን የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ ከሁላችንም የሚጠበቅ ይመስለናል።

የኮቪድ-19 መከሰት የመለስ ዜናዊና የሌንጮ ለታ የእጅ ሥራ የሆነውን ሕገ-መንግሥት ለማሻሻል እና ሕዝባዊ ለማድረግ በር የከፈተ እንደሆነ ስለሚሰማን፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በተሰባሰበ መልኩ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ አማራጭ ሀሳቦችን በማፍለቅ «ሕገ-መንግሥቱ አይነካም» የሚሉትን ወገኖች በነጠረ ሀሳብ ለመሞገት መዘጋጀት ያለብን ይመስለናል።

ችግሮች ለምን ተከሰቱ ወይም ተፈጠሩ ብሎ መነሻቸውን ማወቅ አንድ ነገር ነው። የችግሮቹን መንስዔ አውቆ መፍትሔውን መሻት ደግሞ ዋናውና አስቸጋሪው ተግባር ነው። ያለምን ጥርጥር አገራችን ውስብስብ ችግሮች አሉባት። የችግሮቿ ቋትም የኢትዮጵያውንን ነባር ዕሴቶች፣ አብሮነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ መቻቻል እና የአንድነት ስሜቶችን አጥፍቶ የነዚህ ተቃራኒ በሆነ የተካው ሕገ-መንግሥት ነው።

እያንዳንዱ መጥፎ አጋጣሚ ወይም ችግር፣ የራሱ የሆኑ በጎ ጎኖች አሉት። ይህ የሣንባ ቆልፍ ዓለም አቀፍ በሽታም ከጋረጠው ችግር ጎን፣ በአግባቡ ከተጠቀምንበት፣ የአገሪቱ ችግሮች ቋጠሮ የሆነውን ሕገ-መንግሥት ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ የሚያስችል አጋጣሚ ፈጥሯል ብሎ የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ያምናል። ሕገ-መንግሥቱ መልስ አልባ ያደረገውን ችግር ለመፍታት፣ በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሙያ ማኅበራት፣ የሃይማኖትና የባህል ተቋሞች፣ በአጠቃላይ እያንዳንዱ ግለሰብ በኢትዮጵያ አገራዊ አድንነትና ሉዐላዊነት ጽኑ እና የማይዋዥቅ አቋም መያዝ አለባቸው። ይህን አቋም ከያዙ፣ ከነርሱ የሚጠበቀው ቅንነት፣በጎ አሳቢነት፣ ከግለስብና ከቡድን ፍላጎት ነፃ ሆኖ፣ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚበጁ ሀሳቦችንና አመለካከቶችን

ከየትም አቅጫ ይምጡ የራስ የማድረግ፣በመቻቻልና በሰጥቶ በመቀበል ለወል ውሳኔ ተገዥ መሆን ነው።

ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር እንደሚሉት ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዐላዊነት ዳብሮ መቀጠል ቁርጠኛ አቋም ካላቸው፣ ከእርሳቸው የሚጠበቀው፣ ኢትዮጵያን በካዱ፣ ረጅም ታሪኳን በመቶ ዓመት በገደቡ፣ ተገደው ሳይሆን ወደው ፣አገሪቱን ወደብ አልባ ባደረጉ ባንዳዎች የተዘጋጀውንና ጸደቀ የተባለውን አገር አፍራሽ ሕገ-መንግሥት የችግሩ መፍቻ ሁነኛ መሣሪያ ለማድረግ መጣር፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን እገነባለሁ ከሚሉት ዓላማቸው ጋር ይጋጫል። ምክንያቱም ሕገ-መንግሥቱ የኢትዮጵያን አንድነት ለማፍረስ፣ የሕዝቡን አብሮነት ለመናድ በመሣሪያነት የተዘጋጀ በመሆኑ፣ ቆምኩለት ለሚሉት ዓላማ ማስፈጸሚያ ፈጽሞ አይሆንም። ተደጋግሞ ተሞክሮ ውጤት ባላስገኘ መንገድ መልሶ መሄድም ውድቀትን ያከፋል እንጂ፣ ተፈላጊ ውጤት አያስገኝም። ይህን ይስቱታል አይባልም።

ዶር ዐቢይ ቅንነቱ እና ፍላጎቱ ካላቸው፣ ችግሩን እንዴት መፍታት እንደሚቻል ከላይ የተገለጹትን አቋሞች የሚቀበሉ፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ፣ ከግለሰብ እስከ ድርጅት፣ ከፓርቲ እስከ ማኅበር፣ ከሙያ እስከ ሃይማኖት ድርጅቶች ድረስ ያሉትንና ማንንም ያለገለለ ጉባዔ ጠርተው በማወያየት ለገጠመን አገራዊ ችግር፣አገራዊና ሕዝባዊ መፍትሔ ማፍለቅ የትኩረታቸው ቀዳሚው አጀንዳ ሊያደርጉት ይገባል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ፣ በተለመደው መንገድ በሕዝብ ላይ በኃይል ፍላጎታቸውን በመጫን፣ *ሥልጣንን ብቸኛ የዕውቀት፣ የትክክለኛነት እና ሁሉን ነገር የማድረግ ብቃት ማረጋገጫ አድርገው በመቁጠር፣ እኛ ወይም እኔ ካልኩት ውጪ ምንም ነገር አይሆንም ፤ አይደረግም ፤ በማለት ለውይይትና ለሰጥቶ መቀበል ጎሊናቸውን ዘግተው ሕዝቡን እኔን ተከተል ካሉ፣ የአገሪቱ ችግሮች ከኤቨረስት ተራራ የገዘፈ፣ ከበግ አንጀት የባሰ የተጠላለፈና የተቆላለፈ በመሆኑ እርሳቸውንና አመራራቸውን ጨምሮ ወደ የባሰ የችግር አሮንቃ የሚከተን እንደሚሆነ ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን የምንረዳው ነው።*

ዛሬ፣ እንኳን ተከፋፍለን፣ አንድም ሆነን፣ መፍትሔው ሩቅ ለሆነው የሣናባ ቆልፍ በሽታና እርሱም ላስከተለው «የሕገ-መንግሥት» ችግር፣ ብቸኛ መፍትሔ መንግሥት የሚያራምደው አቋም ነው ብሎ መቆም፣የአመለካከት ብዛኃነትና የሕዝብን ተሳትፎ ዋጋ ከማሳጣት ተለይቶ የሚታይ አይሆንም። ብቸኛ የሥራ ዋስትና መንግሥት በሆነበት አገር፣ መንግሥት ሕይወት ሰጪና ነሺ ፣ ንብረት አከፋፋይና ወራሽ በሆነበትና በዚህም ወዶ ሳይሆን ፈርቶ፣ አምኖ ሳይሆን ተገዶ የመንግሥት ፍላጎት አስፈጻሚ የሆነን፣ ለዓላማ ሳይሆን፣ ሕይወይትን ለማስቀጠል በአዋጅ የተሰበሰበን አባል፣ እንደጥንካሬ ቆጥሮ፣ ሌሎችን ድንክ አድራጎ የመሳል

ዕይታ፣ ዲሞክራሲያዊም ተገቢም ነው ሊባል የሚችል አይደለም። ይህም ገፊ እንጂ፣ ሳቢና አሰባሳቢ አይሆንም። በዚህ ጊዜ ከመሪ የሚጠበቀው፣ አሰባሳቢነት፣ አለኝታነት፣ ሆደ ሠፊነት፣ ትዕግሥትና ቁርጠኝነት ናቸው። ከዚህ በተቃራኒው፣ ሕዝቡንና አገሪቱን ለገጠማት የሕገ-መንግሥት ቀውስ መፍትሔው የብልጽግና ብቻ ነው ማለትና የተለየ ሀሳብ ያቀረቡ ቡድኖችን ማስፈራራት ሕዝቡ ታግሎ ከጣላቸው አመለካከቶችና አሠራሮች የተለየ ነው ለማለት አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን አስፈሪ ነው።

ገዥው ፓርቲ መንግሥታዊ ጡንቻውን በመተማመን፣የተፈጠረውን ሕገ-መንግሥታዊ ችግር የምንፈታው ሕገ-መንግሥታዊ በሆነ አግባብ ብቻ ነው፣ በማለት የራሱን አራት አማራጮች ማለትም (ሀ) አስቸኳይ ጊዜአዊ አዋጅ ማወጅ፣ (ለ) ፓርላማውን መበተን (ሐ) ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል (መ) ሕገ-መንግሥታዊ ትርጉም መስጠት፤ የተሰኙትን አቅርቦ ፣ በብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የደረሰበትን መደምደሚያ፣ ከእርሱ ሀሳብ ጋር የሚስማሙትን ድርጅት መሪዎች በመሰብሰብ ብልጽግና የወሰደውን አቋም እንዲያውቁት ተደርጓል። መንግሥት አገሪቱ የገጠሟትን ችግሮች ለመፍታት የራሱን የቤት ሥራ ሠርቶ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ጠርቶ ማሳወቁ በፊት ያልነበረ አዲስ ጅማሮ በመሆኑ ይበል የሚባል ነው። አጠራሩ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሁሉንም ተቃዋሚ ድርጅቶች አለማካተቱ ትክክለኛ አሠራር ነው ባይባልም፣ መጀመሩ በራሱ ተገቢ መሆኑን ተቀብሎ፣ የተፈጸመው ስሕተት ለወደፊቱ እንዳይደገም በማስገንዘብ፣ የዲሞክራሲያዊ አሠራር ዳዴ እንደሆነ አውቀን ቆሞ እንዲሄድ ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት ነው።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከተሠራው ስሕተት ትልቁ፣ የብልጽግና ፓርቲ በሣንባ ቆልፍ ችግር ሳቢያ የተከሰተውን «የሕገ-መንግሥት» ቀውስ መሻገሪያ ብልሀት ነው ብሎ የደረሰበትን መደምደሚያ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ሲያሳውቅ፣ ለዐማራ ድምፅ ለመሆን የተደራጁትን ድርጅቶች ማግለሉ ነው። ይህ ዛሬ ብቻ ሳይሆን፣ሰኔ 24/1983 ዓም በመለስ ዜናዊ በተጠራው የሽግግር መንግሥት ምሥረታና የዚሁ መንግሥት መተዳደሪያ ቻርተር ማጽደቂያ ጉባዔ ዐማራው ሆን ተብሎ እንዲገኝ አልተደረገም ነበር። «ታሪክ ራሱን ይደግማል» እንደሚባለው ሆኖ፣ ከ28 ዓመታት በኋላም የአገሪቱና የሕዝቡ ዕጣ ፈንታ ምን ይሁን ለሚለው የተደረሰበትን የውሳኔ ሀሳብ ለማዳመጥ አለማጋበዙ የአጋጣሚ ነው ወይስ ሆን ተብሎ? ብለን እንድንጠይቅ አድርጎናል። በእኛ እይታ የአጋጣሚ ነው ለማለት እንቸገራለን። እንደዚህ ያሉ ስብሰባዎች ሲደረጉ፣ መታዬት ያለበት የድርጅቶቹ ጥንካሬና ድክመት ሳይሆን፣ ድርጅቶቹ ቆምንለት ያሉት ሕዝብ ነው። ከሁሉም በላይ የድርጅቶችን ጥንካሬና ድክመት መመዘን ያለበት በሕዝብ እንጂ በተቃዋሚ ወይም ተፎካካሪ ድርጅት አይደለም:: እናም ዛሬ፣

የለውጥ አየር ይነፍሳል፣ በሚባልበት ወቅት ፣የዐማራው መገደፍ አለመቆም ግርምት የሚፈጥር ነው።

በዚህ ዓይነት ጥሎ የማለፍ፣ጊዜ የመግዛት፣ የማድበትና ነጣጥሎ የማዳከም ጉዞ የአገሪቱ ችግሮች ይፈታሉ ማለት ዘበት ነው። አገሪቱን የገጠሟት ችግሮች እንኳን ተከፋፍለንና ተደባብተን፣ ተባብረንና ቀና ሆነንም እልክ አስጨራሽ ትግልን የሚጠይቁን መሆናቸው ግልጽ ነው። ለዚህም በእልክ፣በንዴት፣ በቁጣ፣ በሆደ ባሻነት፣ የምንሰነዝራቸው ሀሳቦች ትግሉን ይጎዳሉ። ኢትዮጵያዊያን «ከመታኝ የሰደበኝ ያመኛል» ብለው የሚያምኑ ስለሆነ፣ አሻካሪ የሆኑ ቃሎችን ላለመናገር ከመጠንቀቅ ባሻገር፣ ተጠያቂነትም ያለብን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። መንገዱ ይህ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ አማራጭ የለም የሚል አነጋገር፤ የሰዎችን ንቃተ-ኅሊና አሳንሶ ከመመልከት በላይ፣ ሰጥቶ የመቀበልን ሂደት የሚፃረር ነው። የዲሞክራሲ ዋልታ የሆነውን መነጋገር፣ መወያየት፣ መደማመጥና ሁሉም የፈለገውን ሳይሆን የሚገባውን የሚያገኝበትን መንገድ የሚዘጋ ነው። እልክ እልክን ይፈጥራል እንጂ፣ አያለዝብም። ቂም ያስቋጥራል እንጂ፣ ፍቅርን አያዳብርም። መነጠልን በማባዛት፣ አንድነትና ኅብረትን ያከሳል። ይህ ደግሞ ለዘመናት ሂደንበት ከዚህ ያደረሰን በመሆኑ ልንደግመው አይገባም።

በጥቅሉ፣ የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት፣ ሰላማዊና ዲሞክራሲዊ በሆነ ትግል የኢትዮጵያ አንድነትና የዐማራ ኅልውና ፀር የሆኑ ቡድኖች በመሣሪያነት እንዲያገለግላቸው የቀመሩት ሕገ-መንግሥት እንዲለወጥ የሚታገል ነው። ሕገ-መንግሥቱ ዐማራው ያልመከረበትና ይሁንታውን ያልሰጠበት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲሰጥም ያልተፈለገበት ነው። ባለፉት 28 ዓመታት በዐማራው ላይ ዓለም አቀፍ ወንጀል የሆኑት፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንዲፈጸምበት ያገለገለ በመሆኑ፣ዐኅኢአድ ይህ ፀረ-ዐማራ ሕገ-መንግሥት እንዲቀየር እና በሌላ እንዲተካ የሚታገል ድርጅት ነው። በዚህ ሕገ መንግሥት መሣሪያነት ከአምስት ሚሊዮን (5,000,000) በላይ ዐማሮች ተገድለዋል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል።

በመሆኑም ስለሕገ-መንግሥቱ የመቀየር ወይም የመሻሻል ጉዳይ እንዲህ ነው ከማለታችን በፊት፣ ሕገ-መንግሥቱ በነማን ተዘጋጀ? እንዴት አዘጋጁት? አዘጋጆቹ ሲያዘጋጁ ፍላጎታቸው (Intention) ምንድነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ መስጠት ለምንደርስበት ድምዳሜ አዎንታዊ መሆን ያስችለናል ብለን እናስባለን።

## 1 ሕገ-መንግሥቱ በነማን ተጋጀ?

የአገራችን ችግሮች ቋት የሆነው «የኢትዮጵያ ፌደሬራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት» የተሰኘው ከዚህ ቅርጽና ይዘቱ ለመድረስ ሁለት ደረጃዎችን አልፏል። የመጀመሪያው ደረጃ፣ ሻዕቢያ፣ ትሕነግ/ሕወሓት እና ኦነግ ማዕከላዊ መንግሥቱን ለመጣልና አገሪቱን በመሸንሸን የየድርሻቸውን ለማንሳት እንዲቻላቸው፣ በተለምዶ «የተሰኔ ማንፌስቶ» የተሰኘው የቃል ኪዳን ሰነድ ነው። ይህ ሦስቱ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዐማራ የሆኑ ድርጅቶች ማዕከላዊ መንግሥትን በእርዳ ተራዳ እንዴት እንደሚያስወግዱትና በምን መልክ እንደሚረዳዱ፣ ማዕከላዊ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ኤርትራ እንዴት እንደምተገነጠል፣ ቀሪዋ ኢትዮጵያን ደግሞ፣ በነገድ (ብሔር/ብሔረሰብ) ሸንሽነው ኢትዮጵያ የምትባለውን አገር፣ ነባር ታሪክና የአደረጃጀት ባህል ቀይረው ፣በነርሱ ፍላጎት የፖለቲካ ሥርዓቱን ለመዘርጋት የተስማሙበት ሰነድ ነው።

ሁለተኛው ደረጃ በሌንጮ ለታ ተረቆ፣ በትሕነግ/ሕወሓት ከፍተኛ አመራሮች ተመርምሮ፣ ታሽቶና ተፈትጎ በሚፈልጉት መንገድ ኢትዮጵያን የሚንድ፣ የትሕነግን/ሕወሓትን አመራር ተከታታይ ትውልድ እስከ መቶ ዓመት ድረስ በሥልጣን ለመቆየት በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ያዘጋጁት ሰነድ ነው። ይህ ሰነድ ትሕነግ/ኢሕአዴግ የተባለው ድርጅት በተሰኔው ማንፌስቶ አማካኝነት በትብብር ማዕከላዊ መንግሥትን አስወግደው ግንቦት 20/1983 አዲስ አበባ ሲገቡ፣ ሰኔ 24ቀን 1983 ዓም በተጠራ «የሽግግር መንግሥት መሥራች ጉባዔ» ፣ለሽግግሩ ዘመን መተዳደሪያ እንዲሆን የጸደቀ ነው። ይህ ጉባዔ 87 አባላት እንዲኖሩት ተደርጎ የተዘጋጀ እንደነበር አይዘነጋም።

የጉባዔውን አባላት በብቸኝነት የመረጠው በመለስ ዜናዊ የሚመራው ኢሕአዴግ የተሰኘው የወያኔ የእጅ ሥራ የሆነው ድርጅት ነው። ይህ «ቻርተር» ም ሆነ ሕገ-መንግሥቱ ሲረቀቅና ሲጸድቅ ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙ ዕድሜ ጠገብ የሆኑት ኢሕአፓና መኢሶን በጠላትነት ተፈርጀው እንዲገኙ አልተደረገም። ከሃምሳ ዓመት በላይ በዘለቀ ተከታታይነት የዳበረው የአገሪቱ ምድርጦ፣ የአየር ኃይል፣ የባሕር ኃይል፣ የፖሊስ ሠራዊትና የደኅንነት አባሎች፣ ከ70ሺ በላይ የኢሠፓ አባላት፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የወጣቶች፣ የሴቶች፤ የከተማ ቀበሌ ማኅበራትና የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ተመራጮች፣ የመንግሥት መዋቅር ሠራተኞች የነበሩ በቻርተሩም ሆነ በሕገመንግሥቱ ረቂቅና ዝግጅት ሀሳብ እንዳይሰጡ የዜግነት መብታቸው በፖለቲካ ውሳኔ ተነጥቀው እንደነበር ይታወሳል።

በሰኔ 24ቱ ጉባዔ የተገኙት የነገድ ድርጅቶች የሚከተሉት ነበሩ::

| ተቁ | የፖለቲካ ድርጅቶች ስም | የተወከሉ ሰዎች ስም | ከተወካዮቹ ከመቶ |
|---|---|---|---|
| 1 | የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር (አነአግ) | 1.1 ሀንፍሬ ዓሊሚራህ<br>1.2 ሡልጣን ዓሉሚራህ<br>1.3 አህመድ ዓሊሚራህ | 3.448% |
| 2 | የቤንሸጉል ሕዝብ የነፃነት ንቅናቄ (ቤሕነን) | 2.1 ዩሲፍ ሀሚድ<br>2.2 ኦቴይብ አህመድ ዳፍላህ | 2.298% |
| 3 | የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አክሽን ግሩፕ (ኢዴአግ) | 3.1ኤፍሬም ዘሚካኤል | 1.494% |
| 4 | የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዲኅ) | 4.1 መሸሻ ብሩ | 1.494% |
| 5 | የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ድርጅት (ኢዴአድ) | 5.1 ሰሎሞን ወዳጆ | 1.494% |
| 6 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢብዴድ) | 6.1 ክፍሌ ወዳጆ | 1.494 |
| 7 | የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢዴመአን) | 7.1 ዓለም እሸት ደግፌ<br>7.2 ሞሐመድ ሰዒድ | 2.298% |
| 8 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) | 8.1 ታምራት ላይኔ<br>8.2 ዳዊት ዮሐንስ<br>8.3 አዲሱ ለገሠ<br>8.4. ታደሰ ካሣ<br>8.5 ሕላዊ ዮሴፍ<br>8.6. ካሡ ዒላላ<br>8.7 ተፈራ ዋልዋ | 10.344% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 8.8 ኃይሌ ጥላሁን<br>8.9 በረከት ስምዖን | |
| 9 | የጉራጌ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ጉሕዴግ) | 9.1 ኃይሌ ወልደሚካኤል<br>9.2.ፋንታሁን ኃይለሚካኤል | 2.298% |
| 10 | የጋምቤላ ሕዝብ የነፃነት ንቅናቄ (ጋሕነን) | 10.1ፔክ ኡጁሉ ፔክ<br>10.2 አጉአህ አሎሞ አፒ | 2.298% |
| 11 | የሐዲያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ሐብዴድ) | 11.1 በዬነ ጴጥሮስ<br>11.2 ቴዎድሮስ ኤፍሬም | 2.298% |
| 12 | የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ (ሐብሊ) | 12.1አብዱል ሰላም አብዱሽ | 1.494% |
| 13 | ሆሪያል | 13.1አብዱላሂ ሐጂ ባሕዶን | 1.494% |
| 14 | የኦሮሞ ነፃነት እስላማዊ ግንባር (ኦነእግ) | 13.1 ሐጂ ኦመር ሞሐመድ እስማኤል<br>13.2 ሰፊያን ጅብሪል ኦማር<br>13.3 ሁሴን ቡኔ ደራራ | 3.448% |
| 15 | የኢሣና ጉራጌ ነፃ አውጭ ግንባር (ኢጉነአግ) | 15.1 አስዌ ብሕዶን ቦወኔ | 1.494% |
| 16 | የከምባታ ሕዝብ ኮንግረስ (ከሕኮ) | 16.1 ተስፋዬ ሐቢሶ<br>16.2 ገብሩ ጴጥሮስ | 2.298% |
| 17 | የኦሮሞ አቦ የነፃነት ግንባር (ኦአነግ) | 17.1 ከሊፋ ሞሐመድ<br>17.2 ሞሐመድ ሢራጅ | 2.298% |
| 18 | የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) | 18.1 ዲማ ነገዎ<br>18.2 ጣሐ አብዱ<br>18.3 ደምሴ ከበደ<br>18.4 አህመድ ሁሴን<br>18.5 ኤ ቢ ጄ ቢያ<br>18.6 ዘገዬ አስፋው<br>18.7 አቢዩ ገለታ<br>18.8 አሊ ዩሱፍ አብዶሽ | 13.793% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 18.9 ጀማል ሮቢሌ<br>18.1o ታደሰ ዳባ<br>18.11 ሌንጮ ለታ<br>18.12 ገላሣ ዲልቦ | |
| 19 | የኦሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦሕዴግ) | 19.1 አሰፋ ጨቦ<br>19.2 መኮንንዶሪ | 2.298% |
| 20 | የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) | 20.1 ኤፍሬም መልካ<br>20.2 ባጫ ደበሌ<br>20.3 ሀሰን ዓሊ<br>20.4 ዲማ ጉርሜሣ<br>20.5 አባዱላ ገመዳ<br>20.6 ዮናታን ኢብሣ<br>20.7 በዳኔ ገዳ<br>20.8 ኩማ ደመቅሣ<br>20.9 አብዱላሂ ሁሤን<br>20.10 ዱጋሣ ደበሌ | 11.494% |
| 21 | የሲዳማ ነፃ አውጭ ንቅናቄ (ሲነአን) | 21.1 ወልደሚካኤል ዱባለ<br>21.2 በተና ሆቴሴ | 2.298% |
| 22 | የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር (ትሕነግ)«ሕወሓት» | 22.1 መለስ ዜናዊ<br>22.2 ተወልደ ወልደማርያም<br>22.3 ክንፈ ገብረመድኅን<br>22.4 ጻድቃን ገብረተንሣይ<br>22.5 ስዬ አብርሃ<br>22.6 ስብሃት ነጋ<br>22.7 ዓለምሰገድ ገብረዓምላክ<br>22.8 ገብሩ አሥራት<br>22.9 ዐባይ ፀሐዬ<br>22.10 ሥዩም መሥፍን<br>22.11 አውዓሎም ወልዱ | 12.643% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 23 | የተባበሩት የኦሮሞ ሕዝቦች ነፃነት ግንባር (ተኦሕነግ) | 23.1 ዋቆ ጉቱ | 1.494% |
| 24 | የወላይ ታሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ወሕዴግ) | 24.1 አልታዬ አላሮ<br>24.2 ሰይፉ ቡቄ | 2.298% |
| 25 | የምዕራብ ሶማሌ ነፃአውጭ ግንባር (ምሶነአግ) | 25.1 አብዱናስር ሸክሳዳሞ ዋሳሜ<br>25.2 መሐመድ ዑጋዝ አብዳ<br>25.3 ዩሱፍ አደም መሐመድ | 3.448% |
| 26 | የሠራተኞች ተወካይ | 26.1 አሰፋ ወዳጆ<br>26.2 ከበቡሽ ቡርኖ<br>26.3 አደፍርስ ወልዴ | 3.448% |
| 27 | የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተወካይ | 27.1 ፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ<br>27.2 ዶ/ር መኮንን ቢሻው | 2.298% |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የሽግግር መንግሥቱን የመሠረቱ እና ቻርተር ያጸደቁ አካሎች በድርጅት ስም ይለያዩ እንጂ፣ ሁሉም አንድ ዓይነት ዓላማና ፍላጎት ያላቸው፣ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነትና ፀረ-ዐማራ ናቸው። በዚህ ስብሰባ የኦሮሞ ሕዝብ በአምስት ድርጅቶች፣ በ28 አባሎች ተወክሏል። የትግራግራይ ሕዝብ፣ በልጁ ትሕነግና የልጁን የትሕነግ/ሕወሓትን ዓላማ ለማስፈጸም በመሣሪያነት ባደራጃቸው፣ ራሱን ትሕነግን ጨምሮ በአምስት ድርጅቶችና በ25 አባሎች ተወክሏል። የቀሩት የነገድ ድርጅቶች ወያኔ/ኢሕአዴግ አዲስ አበባን እንደተቆጣጠረ ለዚሁ ዓላማ ያደራጃቸውና ሕዝቡ የማያውቃቸው የወያኔ ዓላማ አራማጆች እንዲሆኑ በመለስ ዜናዊ የተሰባሰቡ ግለሰቦች ናቸው።

ኢትዮጵያ የሚለውን ስም አስቀድመው፣ በኅብረብሔራዊነት ስም ለጉባዔው የተጋበዙት ድርጅቶች መካከል፣ ሁሉም የትሕነግን ዓላማ የተቀበሉ እና አባላት የሌላቸው የድርጅት ስም ወያኔ ጽሮ ለድምፅ ድጋፍ ያስገባቸው ናቸው። ለምሳሌ «ኢዴመአን» የምርኮኛ ወታደሮች ስብስብ እና በሕወሓት/ኢሕአዴግ የተደራጀና የተመራ ነው። ከጉባዔው በኋላም ኅልው ሆኖ ያልቀጠለ የባንዳ ስብስብ ነው። «ኢዴኅ» በራስ መንገሻ ሥዩም የሚመራና አባላቱ በአጠቃላይ ትግሬ የሆኑበት፣ የፓርቲ ፕሮግራም የሌለው እና ሕወሓትን ለማጀብ የገባ ነው።

«ኢሕዴን» ከኢሕአፓ በከዱ፣ በትውልድ አብዛኛዎቹ ትግሬ የሆኑና በኤርትራዊው በረከት ስምዖን የሚዘወረው ድርጅት ፕሮግራሙን ትሕነግ/ሕወሓት ጽፎ፣ የእርሱን ዓላማ እንዲያራምዱ አስምሎ፣ የወያኔ የዐማርኛ አስተርጓሚ እንዲሆን ያደራጀው ፀረ-ዐማራ ድርጅት ነው።

በክፍሌ ወዳጆ ይመራል የተባለው «አብዴድ» ፣ በሰሎሞን ወዳጆ የሚመራው «ኢዴአድ» እና በኤፍሬም ዘሚካኤል የሚመራው «ኢዴአግ» የተባሉት በወያኔ የውጭ ክንፍ ድርጅት አለን ብለው እንዲገቡና ለጉባዔው መሳካትና ትሕነግ በፈለገው መልክ ጉባዔው እንዲቋጭ ለድምፅ ድጋፍ የገቡ ናቸው። የዚህ ማሳያው ከጉባዔው በኋላ የነዚህ ድርጅቶች ኅልውና የውኃ ሽታ መሆኑ ነው። በሽግግር ዘመኑ የተቸራቸውን ወንበር ተጠቅመው፣ አንዳቸውም ሕዝብ ሰብስበው ስለዓላማቸው ያስረዱ አልነበሩም። ሽግግሩ ሲያከትም የድርጅት ስማቸው አብሮ መቃብር ገባ።

«ጅል ዳኛ የፈረደው ዓመት ያሚግታል» የሚሉት ዕውነት ሆኖ፣ይኸውና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን የሚበትን፣ ዐማራን አገር አልባ እንዲሆን ያጸደቁት የሽግግር ቻርተር፣ የሕገ-መንግሥቱ መሠረት ሆኖ በማገልገሉ አገራችንና ሕዝባችን መውጫ ቀዳደ ላሳጣ ዙሪያ ገብ ችግር ዳርጎናል።

የቀሩት የነደገድ ድርጅቶች፣ ማለትም «ጉሕዴግ»፤«ከሕኮ»፣ኦሕዴግ»፣ «ወሕዴግ»፣ እና «ምሶነአግ» የተሰኙት በፀረ አንድነትና በፀረ-ዐማራነት ከትሕነግ፣ ከኦነግ ፣እንዲሁም ኦነግ ወለድ ከሆኑ ድርጅቶችን ዓላማና ፍላጎት አራማጅ በሆኑ ግለሰቦች ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣ በቻርተሩ አዘጋጆች አውራ ድርጅቶች መሪዎች፣ ተለቅመው «ተደራጁን"እንዲሉ የተደረጉ ናቸው።

እነዚህ በመለስ ዜናዊ ሣንባ የሚተነፍሱ ስብስቦች፣ ኦነግ እና ኦነግ ወለድ የሆኑት ድርጅቶች በጉባዔው ቆይታቸው የሚከተሉትን ወስነው ተነሡ።

(1) የኤርትራን መገንጠል ዕውቅና ሰጡ።

(2) ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንድትሆን ፈቀዱ።

(3) የመንግሥት አደረጃጀት በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ በቁጥር የሚጠሩ 14 የፌደራል አባል ክልሎች እንዲደራጁ ወሰኑ።

(4) በዚህ ውሳኔም ከአንድነትና ከአብሮነት በተቃራኒ፣ ልዩነት እንዲሰበክ፣ ኢትዮጵያዊነትና አብሮነት እንደጠላት እንዲታዩ እና ዘረኝነት እንዲሰበክ በር የከፈተ መንገድ ወለል ብሎ እንዲከፈት አደረጉ።

በዚህ ጉባዔ ከተሰየሙት 84 ሰዎች፣ 25 የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሁለት የሠራተኛ ማኅበርና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን የወከሉ ተቋሞች መካከል ውሳኔውን የተቃወሙት ዕውቁ የቀዶጥገና ሕክምና ባለሙያ የነበሩትና የአዲስ አበባን ዩኒቨርስቲ ከወከሉት አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰር ዐሥራት ወልደዬስ ብቻ ነበሩ። የቀሩት በሙሉ ልባቸው፣ በመለስ ዜናዊ የቀረቡትን የውሣኔ ሀሳቦች ተቀብለው ያጸደቁ ናቸው። የአገሪቱ ችግር መወሳሰብ የሚጀምረውም ከዚህ ውሳኔ በኋላ ነው። ውሳኔውና የውሳኔውን ሂደት ያጸደቁ ሰዎችና ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ መንግሥት ቢኖር፣ በአገር ክሕደት የሚጠየቁ ነበሩ። የጉባዔውን ዝግጅት፣ አጀንዳ ቀረጻ እና የጉባዔውን አመራርና ውጤት ስናጤን የቻርተሩ ባለቤቶች የተሰኔውን ማንፌስቶ የተስማሙት ሻዕቢያ፣ ሕወሓትና ኦነግ እንደሆኑ እንረዳለን። የቻርተሩ መሠረታዊ ሀሳቦች በሌንጮ ለታ የተዋቀሩና በመለስ ዜናዊ ተጠናክረው የተሰነዱ እንደሆነ መረጃዎች በግልጽ ያሳያሉ ።

ይህ ቻርተርና በቻርተሩ ላይ የተመሠረተው ሕገ-መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልመከረበት እና ያልተስማማበት ስለሆነ መለወጥ ወይም መሻሻል አለበት የምንለው ያለምክንያት አይደለም። አገራችን ከ81 በላይ ነገድና ጎሳዎች እንዳሏት ይታወቃል። የሽግግር ቻርተሩን ለማጽደቅ የተገኙት የማንም ውክልና የሌላቸው አሥራ አንድ (11) የነገድ/ጎሣ ተወካዮች ነን ያሉ ናቸው። እነዚም አፋር፣ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ሐረሪ፣ ኦሮሞ፣ ከምባታ፣ ኦሞቲክ፣ሲዳማ፣ትግሬ፣ ወላይታ፣ሶማሌ ናቸው። ስልሳ ዘጠኝ (69) ነገዶች/ጎሣዎች በዚህ ጉባዔ አልተካፈሉም። በሚገርም ሁኔታ በ1987 ዓም የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገሪቱ ሕዝብ 16,007,933 ወይም 30.1% የሆነው ዐማራ፣ 639,556 ወይም 0.12% የሆነው ጌዲዮ፣ 251,233 ወይም 0.98% የሆነው ከፋ ተወካይ እንዲኖራቸው አልተፈለገም። በአንፃሩ ከአገሪቱ ሕዝብ 3,284,568 ወይም 6. 4 % የሆነው የትግሬ ሕዝብ በአምስት ድርጅቶችና በ25 ሰዎች ከመወከሉም በላይ፣ የአገሪቱን የፖለቲካ መዋቅር በብቸኝነት እንዲቆጣጠርና የአገሪቱን ዕጣ ፋንታ በበላይነት እንዲወስን ይህ ጉባዔ ፈቅዶ አስረክቦታል። በሌላ በኩል የኦሮሞ ሕዝብ በኦነግ አማካኝነት ልክ እንደ ትግሬዎቹ ሁሉ፣ «ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ» ዓይነት በአምስት (5) ድርጅቶችና በ28 ሰዎች እንዲወከል ተደርጓል። ቻርተሩም ሆነ በቻርተሩ መሠረትነት የተዘጋጀው ሕገ-መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ አይወክልም፤ ከሁሉም በላይ ዐማራውን በጠላትነት በፈረጁ ኃይሎች የተዘጋጀና የጸደቀ፣በዚህም መሣሪያነት ዐማራው

ባለፉት 28 ዓመታት የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠቂ እንዲሆን ያደረገ ስለሆነ፣ መቀየርና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሕገመንግሥት ይተካ የምንለው ያልምክንያት እንዳልሆነ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል።

## 2 ሕገ-መንግሥቱ በነማን ተዘጋጄ?

ሕገ-መንግሥቱ መሠረት ያደረገው፣ ከላይ በስፋት እንደተብራራው፣ ሰኔ 24/1983 በትሕነግ/ኢሕአዴግ የተጠራው ጉባዔ ያጸደቀው ቻርተር ነው። የዚህ ቻርተር አዘጋጅ ድርጅቶችና ግለሰቦች ማንነት ከላይ በሰንጠረዡ ተመልክቷል። ይህን መነሻ በማድረግ ያዘጋጀው የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን የሚባለው በአቶ ክፍሌ ወዳጆ ኃላፊነት በመለስ ዜናዊ ተመልምለው ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች ተወካይ የሆኑበት የሽግግር ሸንጎ አፈጉባዔ በነበረው፣ዳዊት ዮሐንስ በሚመራው ስብስብ የጸደቀ ነው። ለመሆኑ እነዚህ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ይህን የመሰለ አገር የሚንድ፣ ለዘመናት ክፉ ደጉን ተጋርተው የኖሩትን ነገዶች አጥፊና ጠፊ እንዲሆኑ ያደረገን ሕገመንግሥት ያዘጋጁበት ምክንያቶች ምንድናቸው? ብሎ መጠየቅና ዕውነቱን መሻት፣ ለምንደርስበት የሕገ-መንግሥት መሻሻልና በዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት መተካት አሳማኝ ጭብጥ ይሆናል።

### 2.1 ሻዕቢያ/ ኢሳያስ አፈወርቂ፤

ጀብሓ/ሻዕቢያ ኤርትራ በኢትዮጵያ «ቅኝ ግዛት ተይዛለች፤ ቅኝ ገዥውም ዐማራ ነው» በማለት የመገንጠል እንቅስቃሴ ለ30 ዓመታት ማድረጉ ይታወቃል። ለዓላማው መሳካትም ከፕሮፓጋንዳ እስከ ትጥቅ ትግል አካሂዷል። በዚህም ዐማራውን በጠላትነት ከመፈረጅ አልፎ ፀረ-ዐማራና ኢትዮጵያ የሆኑ ቡድኖችን በማደራጀት፣ በማሰልጠንና በማስታጠቅ የኢትዮጵያን አድነት ሲፈታተን መኖሩ ገሐድ ነው። በተለይም የኢትዮጵያን የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀንዲል ሆና መቆጠር የእግር እሳት የሆነባቸው አካሎች፣ ቀይ ባሕርን ከምንጩ ለመቆጣጠር ከሚሹ አገሮች፣ ቀይባሕርን የዐረብ-ባሕር መሆን አለበት ብለው ከሚያምኑ አካሎች፣በጥቅሉ ከአገሪቱ የሩቅና የቅርብ፣ ታሪካዊና ወቅታዊ ጠላቶች በገፍ ድጋፍ እያከማቸ ኢትዮጵያን ለመበታተን ጠንክሮ መሥራቱ ዓለም ያወቀው፣ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው። እነዚህ አካላት አገራችን በ1888 ዓም ዐድዋ ላይ ባስመዘገበችው ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ድሏ፣ የነጮችን ቅስም የሰበረ በመሆኑ፣ይህን ቂም ለመበቀል፣ ኢትዮጵያን በተለያዩ መንገዶች በማዳከምና በመከፋፈል ሥራ መሰለፍ እንዳለባቸው ወሰኑ። ለዚህም ለአገሪቱ ጠንክሮ መዝለቅ መሠረት የሆኑ ተቋሞች ምንድን ናቸው ብለው ጠየቁ። ለጥያቄአቸውም የሥልጣን

ምንጭና የአንድነት ምልክት የሆነው ዘውዳዊ ሥርዓት፣ የአብዛኛው ሕዝብ ሃይማኖት እና የዘውዳዊ ሥርዓቱ ርዕዮተለማዊ ክንድ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እና ለአገሩና ለሃይማኖቱ ቀናዒ የሆነውን የዐማራ ነገድ መሆናቸውን ተረዱ። እነዚህ ከፈረሱ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም ከሚል ድምዳሜ ደረሱ። ለዚህም ብቸኛው መፍትሔ ለሥልጣን የሚሮጡ ግለሰቦችን፣ የብሔር/ብሔረሰብ ጭቆናን በማጉላት እና ይህን ጥያቄ የሚያነሱ ቡድኖችን በመርዳት ማዕከላዊ መንግሥቱን በማዳከም ኢትዮጵያን ማፍረስ እንደሚችሉ በማመን የተለያዩ የብሔር ድርጅቶች እንዲደራጁ አደረጉ። ጀብሐ/ሻዕቢያ ከያዘው መልከዓምድራዊ አቀማመጥና ከቀዳሚ አደረጃጀቱ በመነሳት የነዚህ ድርጅቶች ቤተ ሙከራ ከመሆን አልፎ፣ ተገን ወደ መሆን ተሸጋገረ። የሻዕቢያው መሪ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በዐማራ ላይ የነበረውን ጥላቻ እንዲህ ሲል ነበር የገለጸው። **«ከዐማራ ሕዝብ አይደለም አብረን መሥራት አብረን መለመን አንችልም።»በማለት፤**

ይህን የኢትዮጵያ ጠላቶች የቀመሩትን ቀመር በ1928 ዓም ላይ የኦስትሪያ-ሀንጋሪ ወኪል ሆኖ በአዲስ አበባ ይኖር የነበረና የቤቶ ሞሶሎን ሰላይ ሆኖ ሢሠራ ተደርሶበት ከአገር የተባረረው ሮማን ፕሮቻስካ የተባለው ሰው፣ **«ኢትዮጵያ፤ የባሩድ በርሚል»** በተሰኘ ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ፣ ኢትዮጵያ የብሐረሰቦች ስብስብ ናት። ሃይማኖቱ፣ ቋንቋው፣ ባህሉ፣ ምግቡ የዐማራ ነው። ሁሉንም ሰብስቦ አስሮ የያዘው ዐማራ የተሰኘው ሕዝብ ነው። ዐማራን ከኢትዮጵያ ላይ ብናነሳው ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም፤ በማለት ጽፎ ያሳተመው መጽሐፍ ከ8 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ከመሰራጨቱም በላይ፣ ምዕራባውያን ኃይሎች የምሥራቅ አፍሪቃና የአፍሪካን ቀንድ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ሲቀርጹ፣ ይህን መጽሐፍ በዋቢነት እያጣቀሱ ነው።

የዚህን መጽሐፍ ዓላማ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴን ከኋላ ሆኖ የሚመራው ጀብሐ/ሻዕቢያ በሰከነ መንገድ የራሱ እንዲያደርገው አደረገ። በመሆኑም ዋለልኝ መኮንን የተባለው በ1962 ላይ «የብሔር ጥያቄ በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ባሰራጨው ጽሑፍ፣ ሮማን ፕሮቻስካ ያለውን በቀጥታ በመገልበጥ ዐማራው ጨቋኝ ብሔረሰብና መደብ እንደሆነ በማተት፣ ዐማራውንና ሥራዐቱን ታግሎ እንዲጥል ለወጣቱ ትውልድ ጥሪ አቀረበ። በዚህ ጥሪ ምክንያትም «መሬት ላራሹ» የሚለውን መፈክር ያነገቡ የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ አራማጆች በአገሪቱ እንደአሸን ፈሉ። ከነዚህ ውስጥ ትሕነግ/ሕወሓት እና ኦነግ ግንባር ቀደምቶቹ ናቸው።

## 2.2 ትሕነግ/ሕወሓት፤

ትሕነግ/ሕወሓት፣ ለትጥቅ ትግል ደደቢት በረሃ ሲወርድ ቀዳሚ ጠላቱ አድርጎ የሳለው ዐማራን ነው። «ዐማራው የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላት ስለሆነ» ሕዝቡ ታግሎ ሊያጠፋው እንደሚገባ ሰበከ። ረጅሙን የኢትዮጵያን ታሪክ እንዲህ በማለት አንቋሸሸ። «ኢትዮጵያ የ3000 ዓመት ዕድሜ ያለው የጋራ ታሪክ የነበራትና ያላት አገር አይደለችም። የኢትዮጵያ ታሪክ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት በመተዳደር በሀገር ደረጃ መቆም ከጀመረችበት ከዳግማዊ ምኒልክ የንግሥና ዘመን ወዲህ የ100 ዓመት ዕድሜ አይሞላውም። --ኢትዮጵያ እንደ አንድ ማዕከላዊ መንግሥት ያላትና ራሷን የቻለች አገር ሆና መቆም በጀመረችበት ወቅት፣ ከኢትዮጵያ ውጬ ኤርትራም በኢጣሊያ ቁጥጥር ሥር በመሆን እንደ አንድ የቅኝ ግዛት አገር ሆና የተፈጠረችበት ሁኔታ እንደነበረ ነው። ---ኢትዮጵያና ኤርትራ ባንድ ወቅት አገር የሆኑ ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ነው» (ሕወሓት 1979 ገጽ 3—7) በማለት ጻፉ፣ አስተማሩ። ታሪኩንም «በውሻ ደብተሮች የተጻፈ ነው» አሉ። የትግራይ ሕዝብ ዐማራን ካላጠፋ ማኅበራዊ ሰላም አያገኝም በማለት የጠላትነታቸው ጥግ የት ድረስ እንደሆነ በግልጽ አሳዩ።

የትግሬ ትውልድ ዐማራውን እንደጭራቅ እንዲያየው የተለያዩ ማጥላያ ስሞችን ከመስጠት በተጨማሪ፣ የኦሮሞ ሕዝብም በጠላትነት እንዲያየውና እንዲያሳድደው፣ ዐማራው በቅኝ ገዥነት፣ በጨቋኝነት፣ በመጤነት፣ በትምክሕተኛነት፣ ወዘተ በመፈረጅ የዘር ዕልቂት እንዲፈጸምበት አደረጉ። ይህን በተመለከተ መለስ ዜናዊ እንዲህ ብሏል።«የትግራይ ሕዝብ ኅልውና በዐማራና በኦሮሞ ቡድን ፍቺ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ላፍታ መዘንጋት የለብንም። መልሰው ጋብቻ የሚፈጥሩበት ፐላት ፎርም ካገኙ ፣ሕወሓት በይፋ ያከትምለታል።» (አማረ ቢሻው 2009 ሽፋን ገጽ)

በዚህና መሰል ፀረ-ዐማራ ጥላቻዎችና ቅስቀሳዎች የትግራይ ሕዝብ ዐማራን እንደሚጠላ ዶ/ር ዓለምሰገድ ዐባይ «አይደንቲቲ ጅልትድ» በተሰኘ ርዕስ ባቀረቡት ጥናት የትግራይ ሕዝብ፣ ከቱርክ፣ ከዐረብ፣ከጣሊያን እና ከዐማራ ማንን ትጠላለህ የሚል ጥያቄ አቅርበው ባገኙት መልስ፣ 82.2% ዐማራን እደሚጠላ አረጋግጠዋል። አቶ አበበ ተጠምቀ የተባሉ የአክሱ ነዋሪ ለዚህ ጥያቄ የሰጡት መልስ «ዐማራና ትግሬ ሁቱና ቱትሲ ነን። ደመኞች ነን።» (ጌታቸው ረዳ 2010- ገጽ40-41)

ይህና መሰል የትሕነግ/ሕወሓት መሪዎች ያሰራጩዋቸው የፕሮፓጋናዳና የትምህርት ጽሑፎችና ንግግሮች ስናጤን ድርጅቱ ትሕነግ/ሕወሓት ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝቡ ፀረ-ዐማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ያደረጉት እንደሆነ መገንዘብ የሚከብድ አይሆንም። በነዚህ ሰዎች የሚዘጋጅ

ሕገ-መንግሥት ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነትና የዐማራውን ኅልውና ያማከለ ይሆናል ማለት «ከእባብ እንቁላላል እርግብ መጠበቅ ነው።»

በዚህም የተነሳ የሕገ-መንግሥቱ መግቢያ ኢትዮጵያ ቀድማ የፀና መንግሥነት እንዳልነበራት፣ አንድ የፖለቲካና ማኅበራዊ ማኅበረሰብ እንዳልገነባች በመካድ፣አንድነቱ ፀንቶ ለዘመናት የኖረውን ሕዝብ ለመበታተን «ሕዝብ» በማለት ፈንታ «ሕዝቦች፣ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች» በማለት አንቀጹን ይከፍታል። ኢትዮጵያን ለመናድ(ለመበታተን) ዋና እና የመጀመሪያ አንቀጽ ሆኖ በመግቢያው የሠፈረው ሀሳብ እንዲህ የሚል ነው። «--የራሳችን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣በነፃ ፍላጎታችን፣በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፣» ይላል። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል የማያውቃቸው ቋንቋን ብቸኛ መሥፈርት ያደረጉ ዘጠኝ ክልሎችና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች እንዲፈጠሩ ተደረገ። ሌሎቹ ክልሎች፣ ከነዋሪው በቁጥር ከፍተኛ ነው የተባለው የክልሎቹ ባለቤትና ባለመብት ሲሆን፣ ዐማራው ይህ መብት እንዳይኖረው ተደረገ። ለምን? ዐማራውን «በመጤነት፣ በምኒልክ ሠፋሪነት፣ በትምክህተኝነት፤ በጨቋኝ ብሔርነት፣ በነፍጠንነት ወዘተ» የተፈረጀ ስለሆነ፣ በተገኘበት ያሻው የፈለገውን እንዲያደርገው በመፈለጉ እንደሆነ ያለፉት 28 ዓመታት በተጨባጨ አሳይተዋል። እናም ሕገመንግሥቱ ፀረ-ዐማራ፣ ፀረ-አንድነት፣ ፀረ- ነባር ዕሴቶች ነው። ኢትዮጵያ ባለፉት ረጅም የኅልውና ዘመኗ ምንም ዓይነት በጎ ታሪክ፣ ባህል፣ እና አንድነትን የሚያጎለብቱ አንዳችም ነገሮች እንዳልተሠሩ የሚክድና፣ አዲስ ማንነት ለመገንባት ዓልሞ የተነሳ ነው።  ይህ ደግሞ ክሕደት ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያን አጥፊ ነው። ኢትዮጵያን የማጥፊያው ሁነኛ መንገድ አድርገው የያዙትም ዐማርን መከፋፈል፣ ማዳከም፣ ታሪኩን ማቆሸሽ፣ እናም ማጥፋት ነው። ከ1983 ዓም ጀምሮ በሐረርጌ፣ አርሲ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቡር፣ ከፋ፣ ጎንደር፣ ወሎ ወዘተ በዐማራው ላይ የተፈጸሙት ጭፍጨፋዎችና ማፈናቀሎች የዚህ ማሳያ ናቸው። የበደኖ፣ አርባ ጉጉ፣ መቻሬ፣ አሰቦት ገዳም፣ ጉራ ፈርዳ ፣ ወልቃይት ፤ጠገዴ፣ ራያ፣ መተክል ወዘተ የፈሰሰው የዐማራ ደም የዚህ ሕገ-መንግሥት ውጤት ነው።

## 2.3 ኦነግ፤

ኦነግ በዚህ ስሙ የተከሰተው ከኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ይሁን እንጂ፣ ሀሳቡ ተጸንሶ የዳበረው «ሜጫ ቱለማ» ከተሰኘው ማኅበር እንደሆነ ይታመናል። የድርጅቱ መሥራቾች የሮማን ፕሮቻስካ ሀሳብ እንዳለ ከመቀበል ዘለው «ዐማራ ኦሮሞን በቅኝ ግዛት ይዟል፤ ዐማራው ነፍጠኛ ነው፣ ኦሮሚያን ለቆ መውጣት አለበት፣ ኦሮሚያ ለኦሮዎች»

በማለት ዐማራውን «መጤና ሠፋሪ» በማለት ነፃ የኦሮሚያ ግዛት ለመመሥረት የተነሱ እንደሆነ ይታወቃል። ለኦነግ ወደዚህ ሀሳብ እንዲያመራ መንደርደሪያውን «ኦሮሞ እና ኦሮሚያ» የሚሉትን መጠሪያዎች ያገኘው በ1840ዎቹ ጀርመን የመካከለኛ አፍሪካን በቅኝ ግዛቱዋ ሥር ለማዋል መቆናጠጫ መሬት ለማገኘት ኢትዮጵያን እንዲያጠና ከላከችው ዮሓን ክራፍ ከተባለ ሰላይ ሚሽነሪ ሀሳብ ነው።

ዮሓን ክራፍ በዘመነ መሣፍንት ዘመን ወደ አገራችን በሃይማኖት ማስፋፋት ስም የገባ የጀርመን ሰላይ ነው። እርሱም መካከለኛውንና ምራዕቡን የአገራችን ክፍል የማኅበረሰብ አኗኗር፣ ሥነ-ልቦና፣ ሃይመኖት እና ግንኙነት በማጥናት ጀርመን አካባቢውን ለመቆጣጠር ያስችላታል ብሎ የደረሰበትን ሀሳብ በመጽሐፍ ጽፎ አሳወቀ። ሀሳቡም የፕሮቴስታንቱ አስፋፊ፣«ቻይናን ስጡንና ኤኽያን የእኛ ትሆናለች» በማለት የተጠቀመበትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ፣ኦሮሞዎችን (በዚያን ጊዜ በዚህ ስም የሚጠራ ነገድ አልነበረም) የእኛ ካደረግን መካከለኛው አፍሪካ የጀርመን ይሆናል ፣ከሚል ድምዳሜ ደረሰ። ይህ ዕውን እንዲሆንም ኦሮሞዎቹ አንድ ዓይነት ባህል፣ ቋንቋ፣ ሥነ-ልቦና አሠፋፈር የሌላቸው ስለሆነ፣ አንድ ዓይነት ቋንቋ እንዲኖራቸው ነገዳቸውን «ኦሮሞ»፣ ቋንቋቸውን «ኦሮሚኛ» ግዛታቸውን «ኦሮሚያ» በሚል ብንተካው፣ ነገዱን ወጥ የሆነ ማንነትና የግዛት አካል እንዲኖረው ስለሚያደርግ አካባቢውን በጀርመን ቁጥጥር ሥር አውሎ፣ መካከለኛው አፍሪካን ለመቆጣጠር የመነሻ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል በማለት ሀሳቡን አሳወቀ። ለሀሳቡ ተፈጻሚነትና ማስፋፊያ እንዲሆን የፕሮቴስታንትን ሃይማኖትን ምዕራብ ወለጋ መሠረት ጣለ። ይህ ሃይማኖትም ለኦነግ ዓላማ ማስፈጸሚያ መድረክ ሆኖ እንደዘለቀ ይታወቃል።

ዛሬ ቋንቋችን "ኦሮሚኛ፣ እኛ ኦሮሞዎች፣ ግዛታችን ኦሮሚያ ነው" የሚለው የኦነግ ትርክት መነሻ መሠረቱ ይህ በዮሓን ክራፍ ለጀርመን ቅን ግዛት መስፋፋት የተነደፈ ሀሳብ ነው። ሀሳቡንም ፖለቲከኞቹ አክረው በመያዝ በተሰኔው ማንፌስቶ፣ በሽግግር ጊዜው ቻርተርና በሕገ-መንግሥቱ የክራንፍ ሀሳብ ዕውን እንዲሆን ተደርጓል። በሮማን ፕሮቻስካ እና በዮሓን ክራፍ አመለካከትና እምነት የተመሩት ኃይሎች ለዐማራው ኅልውና፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ዳብሮ መቀጠል የሚበጅ ተግባር ይፈጽማሉ ተብሎ በፍጹም አይታሰብም። የሆነውም ይኸው ነው። በመሆኑም ሕገ-መንግሥቱ ፀረ-ዐማራ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት ስለሆነ ማሻሻል ምርጫ ሳይሆን ግዴታ መሆን እንዳለበት ዐኅኢአድ ያምናል።

### 3 የአዘጋጆቹ ፍላጎት (Intention) ምን ነበር?

ከላይ በስፋት ለማመላከት እንደተሞከረው የሕገ-መንግስቱ አዘጋጆች መሠረታዊ ፍላጎት(ኢንቴሽን) የኢትዮጵያን ዘመን ጠገብ ታሪክ መሻር፣ ኢትዮጵያዊ አብሮነትን መናድ፣

ዐማራን አገር አልባ ማድረግ፣ ባህላችንና ታሪካችን የማያውቃቸው ማንነቶችን መትከል፣ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ የነበሩ ዕሴቶችን ማጥፋት፣ ቅኝ ገዥ ምዕራባውያን ኃይሎች እንዲጠፉ የዘመቱባቸውን ተቋሞች እንዳያቆጠቁጡ አድርጎ ከሥራቸው መንቀል እንደሆነ ከተሠሩት ሥራዎች፣ ከሚነገሩት ንግግሮች፣ከተጻፉት የፕሮፓጋንዳ ጽሑፎች የምንረዳው ነው።

ባጭሩ የሕገመንግሥት አዘጋጆቹ ፍላጎት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን መናድ፤ ዐማራን አገር አልባ አድርጎ ማሳደድ፣ በማንነቱ እንዳይመካ ማንቋሸሽ፣ ማጥላላትና ማዋረድ እንደሆነ ባለፉት 28 ዓመታት በሕገ-መንግሥቱ መሣሪያነት የተከናወኑት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ተግባሮች አፍ አውጥተው ይናገራሉ።

## 4 ሕገመንግሥቱ ለምን ይቀየር? የሕገመንግሥቱ ችግሮች ምንድናቸው?

1) ሕገ-መንግሥቱ መቀየር ያለበት የመጀመሪያውና ዋናው ነጥብ ከፍ ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው ሕዝብ ያልመከረበት፣ ያልተወያየበት፣ የኢትዮጵያን አንድነት አጥብቀው በሚጠሉ፣ የአገሪቱን ታሪክ በመቶ ዓመት በገደቡ፣ ዐማራውን በነፍጠኝት፣ በወራሪነት፣ በመጤነት፣ በጨቋን ብሔርነት ፈርጀው እና እርሱን ለማጥፋት ፕሮግራም ቀርጸው በተሰለፉ ቡድኖች የተዘጋጀ መሆኑ ዋናው የመሻሻያው ምክንያት ነው።
2) ሕገ-መንግሥቱ ነፃ እና ገለልተኛ ሆኖ፣ በሕዝብ ምርጫ ባልተመረጠ እና የሕዝቡ ሁለንተናዊ ሕይወት መመሪያ የሆነውን ሕገመንግሥት እንዲያጸድቅ መብት ያልተሰጠው መሆኑ፤
3) ሕገ-መንግሥቱ ሲረቀቅ እና ሲጸድቅ በአገሪቱ ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያገባቸውን ኃይሎች በፖለቲካ ውሣኔ የዜግነት መብታቸውን ከልክሎ እና አገራዊ ራዕይ የነበራቸውን ነባር ድርጅቶች ከሂደቱ ያገደ መሆኑ፤ ምሳሌ ኢሕአፓ፣ መኢሰን፣ ኢሠፓ፣
4) ሕገ-መንግሥቱ ለሥልጣን እንዲበቃ የተከተለው የምርጫ መንገድ «አብላጫ ድምፅ» ያገኘ ወይም (First past the post) የሚለው አገሪቱና ሕዝቡ ዝቅተኛ ድምፅ ባገኙ ቡድኖች እንዲመሩ፣ ብዙኃኑ የጥቂቶች ተገዥ ያደረገ በመሆኑ፣
5) የዲሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት መሠረታዊ መርሕና የማዕዘን ደንጋይ የሆኑት የሥልጣን ክፍፍል፣ የዳኝነት ነፃነት፣ የሕገ-መንግሥታዊ ቁጥጥር ሥርዓት እና የመድብለ ፖለቲካ ወይም ፓርቲ ሥርዓትን ሊያሰፍን በሚችል መልኩ ያልተዋቀረ መሆኑ፤

6) የፖለቲካ አወቃቀሩ፣ የኢኮኖሚ አደረጃጀቱና ለብሔር/ ብሔረሰቦች ችግሮች መፍቻ ብሎ የተከተለው ሥርዓት የትሕነግ/ሕወሓትን ፕሮግራም ሥራ ላይ ለማዋል በሕዝባችን ላይ የተጫነ ፀረ-ዲሞክራሲ በመሆኑ፤
7) ሕገ-መንግሥቱ ትሕነግ/ ሕወሓትን ለረጅም ጊዜ በሥልጣን ላይ እንዲቆይ ሆኖ ተጠላልፎ እና ተሰናስኖ የተዘጋጀ በመሆኑ፣ ለዲሞክራሲያዊ ሂደት ታላቅ መሰናክል ነው። ለማሻሻል ቢፈለግ አንድ አንቀጽ ቀርቶ አንድ ቃል ቢወጣ ሕገ-መንግሥቱ እንዳለ የሚናድ ነው። ምሳሌ፣ የሕገ-መንግሥቱ ምሰሶ የሆነው የመግቢያው የመጀመሪያ ሐረግ «እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች» የሚለው «እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ» በሚል ቢተካ፣ የአገሪቱን የግዛት ወሰን የሚደነግገው አንቀጽ 2፣ አንቀጽ 3(2)፣ ሉዓላዊነትን የሚደነግገው አንቀጽ 8(1)፣ የብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት የሚደነግገው አንቀጽ 39(1 እስከ 5) የተዘረዘሩት፣ የፌዴራል ክልሎች የሚደነግገው አንቀጽ 46(1 እስከ 4) የተዘረዘሩት፣ የሥልጣን አወቃቀርና ክፍል የሚደነግገው አንቀጽ 50(1 እስከ 9) የተዘረዘሩት፣ የክልል ሥልጣንና ተግባር የሚደነግገው አንቀጽ 52(1 እስከ 2) የተዘረዘሩት፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላትን የሚመለከተው አንቀጽ 61(1እስከ 2)-- ወዘተ እንዳሉ የሚናዱ ናቸው። ሕገ-መንግሥቱ ዲሞክራሲያዊ አደለም የሚባለውም ለዕድገት፣ ለመሻሻልና ለለውጥ በር የዘጋ በመሆኑ ነው።
8) የዲሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት አስፈላጊ የሚያደርጉት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም አንደኛ፣አገሮቹ በሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ፣ የሕዝቡን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር ፤ ሁለተኛ ፣የባለሥልጣኖችን መብት ለመገደብ ነው። ይህ ዕውን እንዲሆንም፣ የመንግሥት የሥልጣን አካላት ሚዛን በጠበቀና አንዱ ሌላውን ሊቆጣጠርበት የሚችል ዕኩል ሥልጣን ያላቸው ሦስት አካሎች ማለትም ሕግ አውጭ፣ ሕግ-ተርጓሚ እና አስፈጻሚ አካላት እንዲኖረው ተደርጎ መደራጀቱ ለዲሞክራሲያዊ ሂደት መጎልበት አስተማማኝ እንደሆነ ታምኖበት፣ ዲሞክራሲ ሰፍኖባቸዋል በሚባሉት አገሮች እየተሠራባቸው እንዳለ ይታወቃል። ይህ የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት የአገሪቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እንደሆነ በአንቀጽ 50(3) ተደንግጓል። ይህም ሥልጣንን ለዚህ አካል ጠቅሎ ሰጥቷል። ሥልጣን ለሕዝብ ተወካዮች በብቸኝነት ተሰጠ ማለት፣ የሕግ አውጭነቱም፣ የሕግ ተርጓሚነቱንም፣ የአስፈጻሚነቱንም ገዥው ፓርቲ እጅ ገባ ማለት ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ አምባገነን መሆን መሠረቱ ይህ ነው። በሌላም በኩል ሕግ በማውጣት ረገድ ሕዝቡንና የክልል ምክር ቤቶችን አግሏል። ከሁሉም

በላይ ለአስፈጻሚው በምክር ቤቱም ሆነ በሕግ ተርጓሚው እንቅስቃሴው እንዲታይ እና ያሉት የሥልጣን አካሎች ዕኩል ድርሻ እንዲኖራቸው ባለማድረጉ፣ አስፈጻሚው አካል የፈለገውን እንዲያደርግ የፈቀደ በመሆኑ፣ በዜጎች መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት እያስከተለ እንዳለ ያለፍንባቸው የሕገ-መንግሥቱ ዘመኖች ጉልህ ማሳያዎች ናቸው። ምሳሌ የአቶ ስዬ አብርሃ የተከሰሱበት ጉዳይ የዋስትና መብት የሚከለክል እንዳልነበር ይታወቃል። ሆኖም አቶ መለስ ዜናዊ ስዬ ታስሮ እንዲሰቃይ ስለፈለገ ባንድ ቀን ውስጥ ሕግ እንዲለወጥ ተደርጎ ስዬ 6 ዓመት መታሰሩ አይዘነጋም። ይህም ሕግ አውጭውና ሕግ ተርጓሚው የአስፈጻሚው ታዛዦች ሆነው በመደንገጉ እንደሆነ እንረዳለን። የለም ሥልጣን አላቸው እንኳን ቢባል፣ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና ስለሌላቸው ለአስፈጻሚው ታዛዥ እንዲሆኑ ሕጉ ፈቅዷል። ይህ መታረም ያለበትና ሁሉም አካሎች ዕኩል ሥልጣን እንዲኖራቸው፣ ሥልጣናቸውም ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና እንዲኖረው ግድ ይላል።

9) የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 79 (3) «ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ። ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።»ይላል። ይህን ግን እንዳለው በነፃነት ለማከናወን እንዲችሉ ሕገ-መንግሥታዊ ዋስትና አይሰጣቸውም። የዳኝነት ነፃነት ሲባል፣ አሰያየም፣ ዕድገት፣ዝውውር፣ ስንብት ወዘተ ለመሳሰሉት ከሌሎች ቢሮካራሲያዊ አሠራሮች በተለየ፣ ሕጉን እና ኅሊናዬን ብቻ መሠረት አድርጌ ብሠራ እንዲህ እሆናለሁ፣ እንዲህ እደረጋለሁ ብለው እንዳይሰጉ የሚያደርግ ሕገ-መንግሥታዊ ማዕቀፍ ማለታችን ነው። ይህ በተመለከተ ሕገ-መንግሥቱ ሲረቀቅ የአርቃቂ ኮሚሽኑ ዋና ሰው የነበሩት አቶ ክፍሌ ወዳጆ፣ የዳኞች ነፃነት እንዲኖር ሀሳብ አቅርበው፣ አቶ መለስ «ነፃ ዳኝነት ከሆነ ድላችን አሳልፈን ሰጠን ማለት ነው» በማለት እንደመለሰና የዳኝነቱን ተግባር በአስፈጻሚው እጅ እንዲሆን እንዳደረገ ሕገ-መንግሥቱ በግልጽ ያሳያል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሕገ-መንግሥታዊ ትርጓሜ ለዳኞች እና ለሙያተኞች ይሰጥ የሚለውን ሀሳብ መለስ «ትግላችን ለአንድ ድርጅት ሰጠን ማለት ነው» በማለት ተርጓሚው በምርጫ አብላጫ ድምፅ ባገኘ ድርጅት አባሎች ለሚሞላው የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲሆን መደረጉን ሕጉ ያሳየናል። ይህም ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፀር በመሆኑ ሕገ መንግሥቱ እንዲለወጥ ግድ የሚል ነው።

10) ሕገ-መንግሥቱ አገራዊ አንድነትና አብሮነትን ሳይሆን ፣ልዩነትና መነጠልን የሚያበረታታ ነው። አንቀጽ 39፣ 61፣ 62፣ ለዚህ ማሳያዎች ናቸው። በዚህም የተነሳ እስከ ዛሬ የኢትዮጵያዊነት ምልክት ተደርጎ የነበረው የደቡብ ብብሔር/

ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሚገኙት ነገዶች የየራሳቸው ክልል እንዲኖራቸው እየጠየቁ ነው። ሌሎችም በተመሳሳይ መንገድ እየተጓዙ ነው። ይህም የሕገ-መንግሥቱ ችግር ነው።

## 5 ሕገ-መንግሥቱ ምኑ ይሻሻል?

1) ሕገ-መንግሥቱ ምኑ ይሻሻል? ሲባል ከሕገ- መንግሥቱ ውስጥ የቱን ተቀብለን የቱን እናሻሽለው ማለት እንደሆነ ይሰማናል። በዚህ ከተስማማን፣ ከሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው አንቀጾች በምዕራፍ ሦስት ሥር የተጠቀሱት ከአንቀጽ 13 እስከ 38 ያሉት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን የተደነገገው ክፍል ነው። ከዚያ ውጪ ያሉት ጥሬ ካቦች ናቸው። አንዱ አንቀጽ ሲሻሻል ሌላውንም የሚንዱ ናቸው። ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ የሕገመንግሥቱ መግቢያና የሕጎቹ ቁልፍ «እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ፣ሕዝቦች» የሚለው ነው። ይህን ሐረግ፣ **እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ** በሚል መተካት አለበት ብለን እናምናለን ።መተካትም አለበት። ይህ ከሆነ በዚህ መነሻነት ወይም መንደርደሪያነት የተደረደሩት አንቀጾች እንዳሉ ይናዳሉ። በመሆኑም ማሻሻሉ እንደገና የመጻፍ ያህል ይሆናል።
2) በዚሁ የመግቢያው የመጀመሪያ አንቀጽ ላይ «-----በነፃ ፍላጎታችን፣ በሕግ የበላይነትና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሠረተ፣አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፤» የሚለው ኢትዮጵያ የምትባል የባለብዙ ማኅበረሰብ አገር፣ ማኅበረሰቦቿ የሚጋሩት የወል ታሪክ፣ ባህል፣ ሥነልቦና፣ ስሜት እና አብሮነት እንዳልነበራቸው የሚቆጥር፤ የአገሪቱን የረዘመ የመንግሥትነት ታሪክ ከመካድ አልፎ፣ በዘመነ ቅኝ አገዛዝ፣ ቅኝ ገዥ ኃይሎችን በጋራ ታግለው ያሸነፉ የወል ታሪክ እንደሌላቸው የሚቆጥር፣ ነገዶቿ በአንድነት በከፈሉት ዋጋ በአፍሪካ ብቸኛና ነፃ አገርና መንግሥት መሆኗን እንዳልነበር የሸፈጠ (የካደ) ከመሆኑም በላይ፣ በማናቸውም አገርና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ እና መኖርም ያለባቸውን የቋንቋና የአካባቢያዊ ልዩነቶች አስፍቶ አገር ለማፍረስ የገባ ዓላማ ነው። ዓላማውም የሕገመንግሥት አውጭዎቹ ዋና ፍላጎት ነው። ፍላጎታቸውም ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። እናም ይህ ዋና ዓላማ አገር አፍራሽ በመሆኑ እንዲህ ተብሎ እንዲሻሻል እንሻለን። «--በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ፣በነባሩ

መልካም ታሪካችን፣ ባህላችን፣ ማንነታችን፣ አብሮነታችን እና ሥነ-ልቦናችን ላይ መሠረት ያደረገ አንድ ጠንካራ ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ በወል ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፤

3) ከዚሁ ከመግቢያው ሳንወጣ፣ «መጪው የጋራ ዕድላችን መመሥረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፤» የሚለው የተወሰነውን የአገሪቱን አንድ ነገድ ተጠቃሚ፣ ሌሎችን ተጎጅ፣ ግንኙነት አዛቢ ማኅበረሰንና ግንኙነት የተዛባበት ማኅበረሰብ እንዳለ ያሚያሳይ ነው። ዓላማውም አዛቢ የተባለውን በማጥቃት ተዛብቶባቸዋል የተባሉትን አዛቢዎች እንዲሆኑ የቆመ ዓላማ ነው። ይህም በመሆኑ ሕገ-መንግሥቱ በቀለኛ ነው ማለት ነው። ሕግ ደግሞ በባሕሪው በቀልተኛ አይደለም። ፍትሕ እንዲሰፍን ማድረግ እንጂ፤ በመሆኑም በዚህ ላይ በመመሥረት ሕግ አውጭዎቹ ግንኙነት አዛቢ ነው ብለው በፈረጁት የዐማራ ነገድ ላይ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንዲፈጸምበት የሆነው ከዚህ ዓላማ ተነስቶ ነው። በመሆኑም ይህ አንቀጽ እንዳለ መውጣት አለበት እንላለን።

4) አንቀጽ 1 የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜን በሚደነግገው ክፍል «የኢትዮጵያ መንግሥት ፣የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ» ይባል ይላል። ይህ ፌዴራላዊና ዲሞክራሲያዊ የሚለው «መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ» ዓይነት በመሆኑ፣ በተግባር ሰፍኖ ያየነው አናሳዎች በብዙኃኑ ላይ የበላይነት ይዘው የገዙበት፣ ፌዴራላዊ ሳይሆን፣ የከረረና የቀጠነ አኃዳዊነት ገዝፎ የታየበት በመሆኑ ቅጽሎቹ ቀርተው፤ **የኢትዮጵያ ሪፐብሊክ** ቢባል ዲሞክራሲያዊነቱን አያጣም። ምክንያቱም ሪፐብሊክ ሲባል በሕዝብ የሚወከል መንግሥት ማለት በመሆኑ መደራረቡን ያስቀረዋል።

5) አንቀጽ 2 የኢትዮጵያን የወሰን ግዛት የሚደነግገው፣«የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራል አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ፣በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተወሰነ ነው» ይላል። ይህ አንቀጽ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር የፈለገ በመሆኑ፣ የወሰን ክልሏን የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የማያውቋቸውን ትሕነግ/ሕወሓት ሠራሽ ወሰኖችን የኢትዮጵያ የግዛት ማሳያ ወይም ማመላከቻ አድርጎ ደንግጓል። ይህ አንቀጽ ከአንቀጽ 39 ጋር ይጋጫል። አንቀጽ 39 የብሔር ብሔረሰቦችን ባሻቸው ጊዜ የመገንጠል መብት የሰጠ ነው። እናም አንዱ ወይም ሁለቱ በነገዶች ስም የተከለሉ ክልሎች እንገንጠል

ቢሉ፣ የኢትዮጵያ ወሰን የቱ ሊሆን ነው? ባጭሩ አንቀጽ 2ን ከ39 ጋር ስናዛምደው ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር ታስቦ የደነገገ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ተብላ ለዘመናት ለኖረች አገር የራሷ ዓለም አቀፍ ወሰኗ ዓለም በሚያውቃቸው ቋሚ መሥፈርቶች መቀመጥ አለበት እንላለን። በመሆኑም **የኢትዮጵያ የወሰን ክልል፣ ከምድር ወገብ ወደ ሰሜን 3ዲግሪ እስከ 13 ዲግሪ፣ከግሪንዊች ሜሪዲያን መሥመር ወደ ምሥራቅ ከ33 ዲግሪ እስከ 48 ዲግሪ፣ እና ቋሚ ባሕሮችን እና ውቅያኖሶችን መነሻ ባደረገ መልኩ** ወሰኑ በግልጽ መቀመጥ አለበት እንላለን።

6) አንቀጽ 3(2) የሚደነግገው «የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና ሃይማኖቶች በዕኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንጸባርቅ ይሆናል» ይላል። ይህ አንቀጽ ዓርማው ምን እንደሆነ ያልገለጸና ለአስፈፃሚው አካል የፈለገውን እንዲያደርግ ክፍት የተወ በመሆኑ፣ ከመጀመሪያው ስሕተት ነው። በተግባር ግን እንዳየነው፣ ትሕነግ/ሕወሓት ዘመናት ያስቆጠረውን እና ከግማሽ በላይ የሆኑ የአፍሪካ አገሮች የቀለሙን አቀማመጥ እየቀያየሩ የራሳቸው ያደረጉትን አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ከጀርባው ያለው ዐማራና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ነው በሚል ጥላቻ፣ የበርበሬና ጨው መቋጠሪያ አድርጎት እንደነበር ይታወሳል። ይህ በግልጽ እየታወቀ፣ የአንድነት ዓርማን መለስ የሚመራው አስፈጻሚ አካል እንዲመርጥና እንዲወሰን ማድረግ፣ ተገቢም ሕገመንግሥታዊ አሠራርም አይደለም። ሕዝባችን እንደ ሃይማኖቱ የሚቆጥራትን ሰንደቅ ዓላማችን ያለሕዝብ ፍላጎትና ተሳትፎ የተለጠፈውን «ሰማያዊ ቀለምና ባለአምስት ጦር ኮከብ» ሕዝቡ የሚጠራው «አምባሻ»እያለ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል። ከመነሻው እስከ መዳረሻው ስሕተት የሆነ ይህ ዓርማ ተብየ፣ ከሰንደቅ ዓላማችን ላይ መነሳት አለበት እንላለን። ሰንደቅ ዓላማው በራሱ ሙሉ ነው። ሙሉነቱንም እንዲህ ሲል <u>ይተረጉመዋል።«ሰንደቅ ዓላማችን አረንጓዴ ብጫና ቀይ ሦስት ቀለም ናቸው። ምሳሌአቸውም አረንጓዴው ተስፋ፣ ልምላሜና ሀብት፤ ብጫው ሃይማኖት፣ አበባና ፍሬ፤ ቀዩ ፍቅር፣መሥዋዕትነትና ጀግንነት ነው»</u> በማለት አባቶቻችን ቁልጭ አድርገው ያስቀመጡት በመሆኑ፣ ሌላ ድሪቶ ሊጨመርበት አይገባም እንላለን።

7) አንቀጽ 4 የብሔራዊ መዝሙሩን የሚደነግገው የተተወው ለአስተርጓሚው ክፍል በመሆኑ ፣ እርሱም ሕዝብ ሳይወያይበትና ሳይወስንበት የመሰለውን አድርጓል። ይህም ሕገመንግሥታዊ ነው ለማለት እንቸገራለን። ስለሆነም ከሕገመንግሥቱ ዓላማ ተነስቶ የተዘጋጀ በመሆኑ፤ ዓላማው ሲሻሻል ይህም መሻሻሉን የግድ ስለሚያደርገው፤ በዚያን ጊዜ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በሚያዋጡት ሀሳብ ላይ ተመሥርቶ በሙያተኞች ተዘጋጅቶ ሕዝብ በመረጣቸው አካሎች መጽደቅ እንዳለበት እምነታችን ነው።
8) አንቀጽ 8(1) «የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች» የሚለው **የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ነው**! በሚለው መተካት አለበት። ከፍ ሲል እንደተብራራው ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከሚለው ጋር የተያያዙት አንቀጾች ብዙዎች ከመሆናቸውም በላይ የሕገመንግሥቱ አውራ አንቀጾች ናቸው። ስለሆነም ከነዚህ ጋርና እነዚህን መሠረት ያደረጉ አንቀጾች መሻርና በሌላ በተካት አለባቸው።
9) አንቀጽ 39 (1እስከ 5) የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት የሚደነግጋቸው አንቀጾች አገር አፍራሽ ከመሆናቸውም በላይ፣ በየትኛውም አገር ሕገ-መንግሥት ውስጥ ያልታየ አዲስ የጥፋት መንገድ ስለሆኑ፣ አንቀጾቹ እንዳሉ መሰረዝ አለባቸው።
10) አንቀጽ 45 ሥርዓት መንግሥቱን የሚደነግገው «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥራዓተ መንግሥት ፓርላሜናታዊ ነው» የሚለው፣ እስካሁን በተግባር እንደታየው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ምላተ-ሕዝቡ ሳይሆን፣ የሚመርጣቸው የአንድ ምርጫ ጣቢያ ሕዝብ ነው። የአብዛኛውን ሕዝብ ቀርቶ የአንድ ክልልን ሕዝብ ድምፅ ያገኘ አይደለም። ይህም በመሆኑ ሕዝቡ የእኔ ድምፅ ነው ብሎ የሚቀበለው አይደለም። በሌላ በኩል ፓርላሜንታዊ የምርጫ ዘዴ እና የአብላጫ ድምፅ ገዥ መሆን የጥቂቶች ፍላጎትና ጥቅም በብዙኃኑ ላይ የሚጫን በመሆኑ ችግሮች ጎልተው የሚታዩበት ነው። ስለሆነም ሥርዓተ መንግሥቱ ፕሬዜዳንታዊ ሆኖ፣ ፕሬዚዳንቱ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተወዳድሮ በምላተ-ሕዝቡ ተመራጭ እንዲሆን እንሻለን። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት አመራረጥም አብላጫው ድምፅ ያገኙት ሳይሆን፣ ተመጣጣኝ ውክልና ያለው መሆን እንዳለበት ዐኅኢአድ ያምናል።

11) አንቀጽ 46 የፌደራል ክልሎችን የሚወስነው አንቀጽ ከላይ በተደጋጋሚ ባሳየናቸው ተጨባጭ ምክንያቶች ጋር ተያይዞ መውጣት ያለበት እና በሌላ መተካት ያለበት ነው። እንደ ዐኅኢአድ ዕምነት የኢትዮጵያን የመንግሥት ዓይነትና ቅርጽ፣ ፓርቲዎች መወሰን የለባቸውም የሚል የጠነከረ አቋም አለን። ዕምነታችን ያሉት የመንግሥት ቅርጽ ዓይነቶች ማለትም ፌደራላዊ ወይም አሓዳዊ የሚሉት የእያንዳንዳቸው ጥቅምና ጉዳት ለሕዝብ ተብራርቶለትና ተወያይቶበት በሕዝበ ውሣኔ መወሰን አለበት እንላለን። አሓዳዊነት ለምን ከዐማራ ጋር ተያይዞ እንደሚወገዝ ግልጽ አይደለም። የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ቁጥር ወይም ብዛት 193 ነው። ከነዚህ ውስጥ ፌዴራላዊ የሆነ የመንግሥት አደረጃጀት ያላቸው 25 ብቻ ናቸው። 168 አሓዳዊ ናቸው። እናም አሓዳዊ አደረጃጀት አንድ ሃይማኖትን፣ አንድ ቋንቋ፣ የአንድ ዘርን የበላይነት የሚያሰፍን ቢሆን ኖሮ፣ አብዛኞቹ አገሮች ባልተከተሉት ነበር። እናም አሓዳዊነት ለሕዝበ ውሳኔ መቅረብ አለበት። የሕዝቡን ውሣኔ መቀበል ደግሞ ዲሞክራዊያዊ አካሄድ ብቻ ሳይሆን ትክክልና ተገቢም ነው እንላለን። ሕዝቡ የፌደራል አደረጃጀትን ከመረጠ፣ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በክልሎች የተዋቀረ የሚለው፣ **በክፍለ-ሀገሮች (ፕሮቪንስ)** የተዋቀረ ነው በሚለው መተካት አለበት። ምሳሌ ካናዳ። ንዑስ አንቀጽ 2 «ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሠፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ ላይ በመመሥረት ነው» የሚለው **ተሽሮ «በክፍለ-ሀገሮች(ፕሮቪንሶች) የሚዋቀሩት፣ለአስተዳደርና ጸጥታ አጠባበቅ አመች የሆነውን፣ ነባር ግንኙነትና የገበያ ትሥሥር ያላቸውን፣ ለተፋጠነ ዕድገትና ልማት አመቺነት ያለውን፣ ተመሳሳይ ሥነ-ልበና፣ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ባህል እና የኢኮኖሚ አደረጃጀት መሠረት በማድረግ ነው፤** በሚለው መተካት አለበት።

12) አንቀጽ 47(1 እስከ 4) እና አንቀጽ 48 (1 እስከ 2) የተዘረዘሩት ከአንቀጽ 46 ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ ስለሆነ ፣ይህ አንቀጽ በተሻሻለበት መንገድ የሚሻሻሉ ናቸው።

13) አንቀጽ 49 ስለርዕሰ ከተማ የሚደነግገው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግሥት ይሆናል» የሚለው ፣ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለመረጠው የአዲስ አበባ ሕዝብ ነው፤** በሚለው መተካት አለበት። ንዑስ አንቀጽ 5 ስለኦሮሚያ

ልዩ ጥቅም የሚደነግገው አንቀጽ ያላንዳች ማሻሻያ መሰረዝ አለበት። በአንዲት አገር ውስጥ ያሉ ነገዶች አንዱ ለልዩ ጥቅም ከፋይ፣ ሌላው ተካፋይ መሆኑ የግጭት መንስዔ እንጂ፣ አንድነትና ትብብርን አዳባሪ አይሆንም። አዲስ አበባ የተገነባችውም በሁሉም ነገዶች ጥረትና ሀብት ነው። እንዳውም ነገሩን አጥርተን ካየነው፣ከአዲስ አበባ መገንባት ተጠቃሚው ልዩ ጥቅም ፈላጊው ነገድ ነው። በትምህርት፣ በጤና፣ በመገናኛ፣ በገባያ፣ በኃይል ማመንጫ ወዘተ ከሌሎች ክልሎች የበለጠ ተጠቃሚው ልዩ ጥቅም ፈላጊው ነው። ከዚህ ሌላ ልጠቀም ማለት የጤና አይመስለንም።

14) አንቀጽ 50 (1እስከ 9) ያሉት ከፍ ሲል የተጠቀሱት ማሻሻያዎች ጋር ተያይዞ የሚሻሻል እንደሆነ በመገንዘብ፤ ንዑስ አንቀጽ 3 «የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌደራሉ መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ነው» የሚለው የሦስቱን የመንግሥት ቅርንጫፎች ማለትም ሕገ አውጪውን፣ ተርጓሚውን እና አስፈጻሚውን ዕኩል መብትና ሥልጣን እንዳይኖራቸው ፣ሁለቱ ቅርንጫፎች በሕግ አውጭው ሥር እንዲሆኑ ያደረገና ለሚመረጠው ፓርቲ ሰብሳቢ(ሊቀመንበር) ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን የሰጠ ስለሆነ መቀየር አለበት። ሦስቱም የመንግሥት ቅርንጫፎች ዕኩል ሥልጣንና መብት እንዳላቸው መረጋገጥ አለበት። አንድ ቅርንጫፍ የበላይ መሆን ተገቢና ዲሞክራሲያዊ አይደለም። እናም አንቀጹ ሦስቱንም ቅርንጫፎች በዕኩል ሥልጣን በሚሰጥ መተካት አለበት። ይህም **የኢትዮጵያ ሪፐብሊክ የመንግሥት ከፍተኛ አካላት የሆኑት ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና አስፈጻሚ ዕኩል ሥልጣን አላቸው። ሕግ አውጪው ሕግ ያወጣል። የወጣውን ሕግ ተርጓሚው ይተረጉማል። አስፈጻሚው ያስፈጽማል።** አንዱ ሌላውን ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ውጪ እንዳይሠራ ይቆጣጠራል። በሚለው መንፈስ መተካት አለበት።

15) አንቀጽ 53 ስለ ፌዴራል መንግሥት ምክር ቤቶች የሚደነግገው፣ «የፌዴራሉ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል፤ እነዚህም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች ናቸው» የሚለው **የፌዴራሉ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል፤ እነዚህም የሕግ መወሰኛ እና የሕዝብ ተወካዮች ናቸው።** በሚለው መተካት አለበት። ይህም በመሆኑ የተቋሞችን ተከታታይነት ይጠብቃል።

16) አንቀጽ 59 «በዚህ ሕገ መንግሥት በግልጽ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምጽ ነው።» የሚለው የአገርና የሕዝብ መብቶችና ጥቅሞችን በአብላጫ ድምፅ መወሰን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የተወሰኑ ቡድኖችን ዓላማ ለማስፈጸም ይውላል። ነገሮች ሳይብራሩ፣ ጠንካራ መረጃዎች ሳይቀርቡ፣ ሕግ ሆነው እንዲወጡ ሠፊ በር ይከፍታል። ይህ እንዳይሆን፣ የሕጎቹ ዓይነቶች መለየት ይኖርባቸዋል። መሠረታዊ፣ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑ ካልሆኑት መለየት አለባቸው። መሠረታዊዎቹ በሁለት ሦስተኛ፣ መሠረታዊ ያልሆኑት በአብላጫ ድምፅ እንዲወሰኑ መደረግ አለበት። ሕጎቹም ሲጸድቁ በተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ሳይሆን፣ በሁለቱም ማለትም በሕግ መወሰኛውና በሕዝብ ተወካዮች በተናጠልና በጋራ በሚያደርጉት ክርክር ላይ ተመሥርቶ መሆን አለበት። ምሳሌ የአሜሪካ ሴኔትና ሕዝብ ተወካዮች በጋራ ነው ሕጎችን የሚደነግጉት። ይህ ሁሳብ የቀረበው፣ የአሁኑ የምክርቤቶች አደረጃጀት የሚለወጥ ከሆነ ነው። መለወጥም አለበት ብለን እናምናለን።

17) አንቀጽ 60(1) «ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ፣ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል።» የሚለው የሚከተሉት ችግሮች አሉበት። (ሀ) «አዲስ ምርጫ ለማከሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ እንዲበተን ያደርጋል» የሚለው ፈቃደኝነትን እንጂ፣ ሕጋዊነትና አስገዳጅነትን አያመለክትም። ፈቃደኛ ባይሆንስ? ፈቃደኛ ሆኖ ራሱን ካልበተነ አዲስ ምርጫ አይደረግም ማለት ነው። ካልተደረገ ደግሞ በየአምስት ዓመቱ ምርጫ ይደረጋል የሚለው ተግባራዊ ላይሆን ነው። (ለ) ምርጫ በሚደረግበት ዘመን ምርጫን ማካሄድ የማይቻልበት ሁኔታ ቢፈጠር ምሳሌ እንደ ኮቪድ-19 (ሣምባ ቆልፍ) ፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ጦርነት ቢከሰት ምን መደረግ እንዳለበት የመፍትሔ አቅጣጫ አያሳይም። በመሆኑም ይህ አንቀጽ **(1) ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት፣አዲስ ምርጫ ለማካሄድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ያደርጋል፤ ተብሎ መሻሻል አለበት። (2) ምርጫን ለማካሄድ የማያስችሉ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች ሲከሰቱ፣ በብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጥያቄ አቅራቢነት፣ ምክር ቤቱ ሙያተኞችን አወያይቶች ከተከሰተው ችግር ጋር ተመጣጣኝ ለሆነ ጊዜ ሥልጣኑን ማራዘም ይችላል።** የሚል አንቀጽ መጨመር አለበት።

18) አንቀጽ 61፣62 እና 63 የተዘረዘሩት ጉዳዮች መሠረታዊ ፍላጎት፣ የብሔረሰቦች መብት እና ዕኩልነት ማረጋገጫ እንዲሆን ከሚል እሳቤ የገቡ አንቀጾች እንደሆኑ እናስባለን። ይሁን እንጂ፣ የብሔረሰቦችን ዕኩልነት ዋና ማረጋገጫ በሆነው የሕግ ማውጣትና ማጽደቅ ሂደት ሚና እንዳይኖረው የተደረገ ተቋም በመሆኑ የታለመለትን ዓላማ እያሳካ አደለም። ያ! ቢሆን ኖሮ፣ በዐማራ፣ በአኞዋክ፣ በሶማሌ፣ በጉራጌ --ወዘተ ነገዶች ላይ፣ ከዘር ማጥፋት እስከ ዘር ማጽዳት፣ማፈናቀልና ማሳደድ ያሉ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ተቋሙ በችልታ አይመለከትም ነበር። በእኛ እይታ ይህ ተቋም የታለመለትን የነገዶች ዕኩልነት ጠበቃ እንዲሆነ ሕግ የማውጣትና የማጽደቅ ሚና እንዲኖረው ይገባል እንላለን። ለዚህም አባላቱ «ከፍለሀገር» ወይም ፕሮቪንስ ያሉትን ነገዶች ምጣኔ ግምት ውስጥ ያስገባ እና እያንዳንዱ ክፍለ-ሀገር እኩል መጠን ባላቸው ሰዎች መደራጀት ይኖርበታል። ይህም ማለት አገሪቱ 15 ክፍለሀገሮች(ፕሮቪንሶች) ቢኖሯት፣ እያንዳንዱ ዕኩል ቁጥር ያላቸው ሰዎችን ይመርጣሉ። ምሳሌ ዐሥር ዐሥር ሰዎች ይወከሉ ብንል፣ ይህ አካል 150 አባላት ይኖሩታል ማለት ነው። አካሉ በሕግ ማውጣትና ማጽደቅ ሂደት ወሣኝ ሚና እንዲኖረው መደረግ አለበት እንላለን። ሌሎቹ ስለፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚያወሱት አንቀጾች ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተያይዘው የሚታዩ ናቸው።

19) አንቀጽ 74(13) ጠቅላይ ሚኒስትሩ«ሕገ-መንግሥቱን ያከብራል፣ ያስከብራል» የሚለው ሕገ-መንግሥቱን የማስከበር ጉዳይ የሁሉም ቅርጫፎች የመንግሥት አካላት እና የሕዝቡ ጭምር መሆን አለበት። ከሁሉም በላይ የፍትሕ አካላቱ ሚና ሕገ-መንግሥቱንና ሕገ-መንንግሥታዊ ሥርዓቱን ሕግን ከመተርጎም ጀምሮ የማስከበር ኃላፊነት የርሱ መሆን አለበት። ይህን አንቀጽ ሕገ-መንግሥቱን በማስከበር ስም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አምባገነን እንዲሆን በር የሚከፍት ስለሆነ መውጣት አለበት።

**20)** አንቀጽ 75 የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን ተግባር የሚገልጸው ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሆነ ምክንያት ኃላፊነታቸውን መወጣት ባይችሉ ማን ሊተካቸው እንደሚችል በግልጽ የተቀመጠ ሕግ የለም። በመሆኑም በዚህ አንቀጽ ሥር የሚከተሉት አንቀጾች መጨመር አለባቸው እንላለን። **(1) ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሆነ ምክናያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ፣ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ኃላፊነት ይወስዳል። (2) ጠቅላይ ሚኒስትሩና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሆነ**

**ምክንያት ኃላፊነታቸውን መወጣት ባይችሉ፣ የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ኃላፊነቱን ይወስዳል።**

21) አንቀጽ 83 ሕገመንግሥትን ስለመተርጎም የተደነገገ ነው በአብዛኛዎቹ አገሮች ሕገመንግሥት የመተርጎም ኃላፊነት የተሰጠው ለሕግ ተርጓሚው አካል ነው። በዚህ ሕገ-መንግሥት የሕገ-መንግሥት አጣሪ በአንቀጽ 82 የተደነገገው የሕግ ሙያተኞችን ያካተተ እንደሆነ ቢያሳይም፣ እነዚህ ከፖለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛነታቸው በግልጽ የማይታወቅ ከመሆኑም በላይ የሚሰጡት ውሳኔ ገዥነት የለውም። ሕገ-መንግሥቱን በወሣኝነት የመተርጎም ሥልጣኑ በፖለቲካና በነገድ በተሰባሰበው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በመሆኑ፣ ትርጉሙ ከሕግ አግባብ ብቻ ይተረጉማል ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። በመሆኑም ሕገ መንግሥቱን የመተርጎሙ ሥልጣና ለሕግ ተርጓሚው መሰጠት አለበት።

22) አንቀጽ 104 «የሕገመንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ ስለማቅረብ» በሚለው ሥር የማሻሻያ ሀሳብ ለማመነጨት በራሱ፤ (1ኛ) የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤትን ሁለት ሦስተኛ (2/3) ፣ (2ኛ) የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላትን ሁለት ሦስተኛ(2/3)፣ ወይም ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች አንድ ሦስተኛ(1/3) (ይህም ማለት አሁን ባለው የክልሎች ብዛት 3 ክልሎች) ድጋፍ መስጠት እንዳለበት የሚያስገድድ ነው። ይህ እንግዲህ የማሻሻያ ሀሳብ ለማመንጨት ነው። ይህን ለማግኘት ከመጀመሪውኑ የሀሳብ አቅራቢዎችን የማድረግ ፍላጎት አስቀድሞ የማይገፋ ተራራ አድርጎ ያቀረበ በመሆኑ፣ ሕጉን ያዘጋጁና ያጸደቁ አካላት ፣ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻል ቀና ፍላጎት ያልነበራቸው እንደሆኑ ያሳያል። የማይሻሻል ሕገ-መንግሥት ደግሞ ማኅበራዊ ሰላም፣ተከታታይነት ያለው ዕድገትና ብልጽግና እንዳይኖር ከፍተኛ እንቅፋት ነው። ከሕዝብ ፍላጎትና ምኞት ጋርም የሚፃረር ነው። ስለሆነም ይህ አንቀጽ ለሚፈለገው ሰላም እና ዕድገት ጠቃሚ ባለመሆኑ በሚከተለው መልኩ መሻሻል አለበት። **ሕገ-መንግሥት ለማሻሻል የሚቀርብ ሀሳብ በተወካዮች ምክር ቤት የአብላጫ ድምፅ ማግኘት አለበት፤**

23) አንቀጽ 105 ሕገ-መንግሥት ስለማሻሻል የሚደነግገው የሕገመንግሥቱ ክፍል ነው። በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ «በዚህ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩት መብቶችና ነፃነቶች በሙሉ፣ ይህ አንቀጽ እንዲሁም አንቀጽ 104 ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ነው። (ሀ) ሁሉም የክልል ምክር

ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምፅ ብልጫ ሲያጸድቁት፣ (ለ) የፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቀው፣ (ሐ) የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያፀድቀው።» ይህ ሲሆን ብቻ በአስቸጋሪም ሁኔታ ወይም በአጋጣሚ ወይም በዕድል ምክንያት የመነጨን የማሻሻያ ሀሳብ ለማጽደቅ ከላይ የተዘረዘሩትን ከፍተኛና አስቸጋሪ ማነቆዎች ማለፍ ይኖርበታል። ይህ አንቀጽ፣ የሕግ አውጭዎቹን ቡድኖች ዋና እና ተቀዳሚ ፋላጎት ገላጭ ነው። ቡድኖቹ ለረጅም ዓመታት ለመግዛት መሣሪያ የሆናቸው ሰነድ እንዲሻሻል ፍላጎት ፈጽሞ የሌላቸው መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው። ማሳያውም በአገሪቱ ከፍተኛው የሥልጣን አካል የተወካዮች ምክር ቤት መሆኑን ደንግጎ፣ ሕግ የማውጣትም ሥልጣን የዚሁ አካል መሆኑን አረጋግጦ፣ ወደ ማሻሻል ሲመጣ፣ በፌደራል ደረጃ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያልተሰጣቸውን አካሎች ማለትም የክልል ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምፅ እንዲወስኑ፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን እንዲያጸድቁት ይጠይቃል። ይህም በመጀመሪያ ተቃርኖ ይታይበታል። ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያልተሰጣቸውን አካሎች፣ ሕግ እንዲያሻሽሉ ሳይሆን፣ በተቃራኒው የመነጨ ሀሳብ ፣ሕግ ሆኖ እንዳይወጣ ሥልጣን ሰጥቷል። ይህ ቅራኔ ነው። በሌላም በኩል ሕግ ከማውጣትና ከማሻሻል የቱነው ከባዱ? ብለን እንድንጠይቅ ይጋብዘናል። በዚህ ሕገ-መንግሥት ዕይታ ሕግ ማውጣት ቀላል፤ ማሻሻል ከባድ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ለመሆኑ ይህ አንቀጽ ያሳያል። ከባድ እንዲሆን የተፈለገውም ሕገ-መንግሥቱ እንዳይሻሻል ትሕነግ/ሕወሓት ለመቶ ዓመታት በሥልጣን ላይ እንዲቆይ የታቀደ ስለሆነ ነው። እንደ ዐኅኢአድ እምነት የቀረበን ማሻሻይ ሀሳብ የማጽደቅ ሥልጣን የሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ መሆን አለበት እንላለን። እና ማሻሻያው **የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴዴሽን ምክርቤት(የክፍለ-ሀገራት-ሕገ-መወሰኛ) በጋራ ተሰብስበው በሁለት ሦስተኛ ድምፅ መጽደቅ አለበት፤** በሚለው መተካት አለበት እንላለን።

24) አንቀጽ 105(2) በ(ለ) ሥር የተጠቀሰው ተሰርዞ በ(ሀ) ያለው ብቻ ሕጎቹን ለማሻሻል በቂ ነው እንላለን።

## 25) ማሳሰቢያ፤

25.1 ከመግቢያችን ላይ እንዳልነው፣ በሂደትም አንቀጾቹን እየጠቀስን እንዳሳየነው፣ ሕገመንግሥቱን ከማሻሻል መለወጥና በአዲስ መልክ ማዘጋጀቱ እጅግ ጠቃሚና ተመራጭ እንደሚሆን እንገነዘባለን። ይህን ስንል «ሕገመንግሥቱ አይነካም እርሱ ከተነካ አገር ትፈርሳለች» የሚሉ ቡድኖች መኖራቸውን ረስተን ወይም ዘንግተን አይደለም። የሕገ መንግሥት ጉዳይ የቡድኖች ወይም የፓርቲዎች ሳይሆን፣ የሕዝቡ እንደሆነ ስለምናምን ነው። እናም ሕዝቡ በነቂስ ቢጠየቅ ይህ ሕገ-መንግሥቱ ለያይቶናል፤ ነጣጥሎናል፤ ደም አቃብቶናል፤ አንድነታችን ጎድቶታል፤በማለት ይለወጥ እንደሚል ጽኑ እምነት ስላለን ነው።

25.2 ሕገመንግሥቱን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች «አማራጭ አምጡ፣ ወይም አማራጭ ሀሳብ የላቸውም» የሚባሉት መልሶች ዲሞክራሲያዊም ሕዝባዊይም አይደሉም። አማራጭ የሕገ-መንግሥት ሀሳብ አምጡ ማለት የአንድ ድርጅት ፍላጎት ሕዝብን ይግዛ ከማለት አልፎ ድርጅቶች የእኔ የእኔ በሚል ፍትጊ ውስጥ እንዲገቡ የሚገፋፋ ነው። ሕገ-መንግሥት መዘጋጀት ያለበት ሕዝቡ የኔ ናቸው፣ ለአገራችን ዕድገትና የተረጋጋ ማኅበራዊ ሰላም ሊያሰፍን የሚችል ሕግ ማዘጋጀት ይችላሉ ብሎ፣ ድምፁን በሚሰጣቸው የሕግ አርቃቂና አጽዳቂ ኮሚሽኖች መሆን አለበት። በዚህ ሂደት የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች ወዘተ ሊኖራቸው የሚችለው ሚና፣ ያለው ሕገ-መንግሥት ያሉትን ችግሮች እና ክፍተቶች ነቅሶ ማሳየት፤ ለሕገ-መንግሥቱ አዘጋጆች ግባት ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ማዋጣት ነው። በዚህ ረገድ የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(ዐኅኢአድ) ከላይ የሰነዘራቸው ሀሳቦች ብቸኛ የሕጉ አካላት ይሁኑ የሚል ሳይሆን፣ በሕዝብ አደራ ለሚሰጠው የሕግ አርቃቂና አጽጋቂ ኮሚሽን ግባት እንዲሆኑ፣ በሥልጣን ላይ ያለው የብልጽግና ፓርቲም የችግሮቹን ግዝፈት ተመልክቶ፣ ወደ መሃል በመምጣት የችግራችን ቋጠሮ የሆነው ሕገ-መንግሥት እንዲለወጥ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ለማሳሰብ ነው።

## 6 ምርጫን ማራዘም ያስከተለውን የሕገ-መንግሥት ቀውስ ለመሻገር የዐኅኢአድ አቋም።

በዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(ዐኅኢአድ) ዕይታ፣ ከብልጽግና ፓርቲ ውጭ ያሉ ድርጅቶች የአቀራረብ ቅርጻቸው ይለያይ እንጂ፣ ጥያቄአቸው እኛም ተሳታፊ የምንሆንበት የሽግግር ሥርዓት ወይም መንግሥት ይቋቋም የሚል ነው። ይህ ጥያቄ የዐኅኢአድም የቆዬ ጥያቄ ነው። በየትኛውም መልኩ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። መቅረብም አለባቸው። የቀረቡ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ደግሞ ሁሉም ትክክልና ተገቢ ናቸው አይባሉም። የቀረቡትን ሀሳቦች ትክክለኛነትና ተገቢነት የሚወስነው በዕኩል መቀመጫ ተቀምጦ፣ ለቀረቡ ሀሳቦችና ጥያቄዎች በሚሰጡ መልሶችና በሚቀርቡ ማስረጃዎች ትክክለኛነትና ተጨባጭነት፣ ሌላውን አካል የማሳመን ብቃት የመጀመሪያው ደረጃ ነው። ሁለተኛው ሀሳቦቹንና ጥያቄዎቹን የዳመጠው አድማጭ ሕዝብ ወይም ቡድን የሚደርስበት የአብላጫ ሀሳብ ነው። ከዚህ ውጭ የእኔ ሀሳብ እና ጥያቄ ትክክል ነው የሌሎች ስሕተት ነው ማለት «ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ» የሚሉት የአባቶቻችን ይትባህል ከመሆን አልፎ ተገቢም ትክክልም አይሆንም።

ባሁኑ ሰዓት አገሪቱ ከገጠማት ዓለም አቀፍ የሣንባ ቆልፍ ወረርሽኛና መንግሥት ተጋርጦብኛል ከሚለው የቀጣና የፀጥታ ችግር አንፃር ሲመዘን፣ «የሥልጣን እንጋራ» ጥያቄ ሕዝባዊና አገራዊ አጀንዳ ነው ለማለት ያስቸግራል። በየትኛውም ሂደት የቅደም ተከተል ጥያቄ አለ። በመሆኑም በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ መቅደም ያለበት፣ የሕዝቡ ጤንንት መጠበቅ፣ ሰላሙና ደኅንነቱ መረጋገጥ፣ የአገሪቱ ግዛታዊ አንድነት እና ሉዓላዊነት መጠበቅ የሚለው እንደሆነ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። ሥልጣንና ምርጫ እነዚህ ከተረጋገጡና በነዚህ ላይ ያነጣጠሩ ችግሮች መወገዳቸው ሲረጋገጥ በሰከነ መልኩ የሚነሱ ናቸው። ሕዝብ ሳይኖር ሥልጣን፣የሕዝብ ደኅንነትና የአገር ሰላም ሳይረጋገጥ ምርጫ  ማካሄድ ችግርን ከማባባስ ውጪ ችግር ይፈታል አይባልም።

በመሆኑም ዐኅኢአድ ሕገ-መንግሥቱ የሕዝብ አይደለም፤ ዐማራውንም አይወክልም፤ የሚል አቋም ይዘን ለሕገ-መግሥት መለወጥ፣ ወይም መሻሻል የምንታገል መሆናችን በግልጽ ይታወቃል። ይህ በሥራ ላይ ያለ ሕገ-መንግሥት በእኛ እይታ ተጠጋግኖ የማይድን ፣አንዱ አንቀጽ ሲነሳ ጠቅላላውን የሚናድ መሆኑን ስለምንገነዘብ፣ ከሣናባ ቆልፍ ወይም ኮቪድ-19 የተባለው ዓለማ አቀፍ ተላላፊና ሕይዎት ቀሳፊ የሆነው ወረርሽኝ ባስከተለው የምርጫ ጊዜ መራዘምና፣ ይህም ባስነሳው ሕገ-መንግሥታዊ ጥያቄ፣ ከተለያዩ አካሎች የተሰጡ ሀሳቦችን በአጽንዖት ተከታትለናል። የተሰጡትን ሀሳቦችም እናከብራለን። ዲሞክራሲ ከመነሻው

የተለያዩ ሀሳቦች የሚነሱበትና የሚደመጡበት ከዚያም ሕዝቡ የሚገዛው ሀሳብ ወሳኝ የሚሆንበትን ሂደት የሚከተል በመሆኑ፣ የሀሳቦቹ መነሳት ትክክልና ተገቢም ነው እንላለን። **በመሆኑም የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ፣ ከመስከረም በኋላ በሥልጣን ላይ ሊያስቀጥለው የሚችለውን የመረጠውን መንገድ ተጠቅሞ፤ ለአንድ ዓመት ጊዜ ሥልጣኑን አራዝሞ እንዲቀጥል የተከተለውን አካሄድ ይደግፋል፤ ይቀበላል። ገዥ ፓርቲና መንግሥት ለአንድ ዓመት ጊዜ ሥልጣኑን እንዲያራዝም ድጋፋችን የምንገልጸው፣ በተራዘመለትን የሥልጣን ዘመን ውስጥ የሚከተሉትን እንዲያከናውን ታሳቢ ብቻ ሳይሆን ግዴው እንደሆነ አድርጎ እንዲሠራ ከመጠየቅ ጭምር ነው። እነዚህም** ፦

1) ለዲሞክራሲያዊ ሂደት መጎልበትና መጠናከር መሠረት የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች ማለትም የፍትሕ አካላትን፣ የምርጫ ሕግና የምርጫ በርድን፣ የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችን አጠቃቀምና አሠራር፣ ወዘተ ከፖለቲካ ገለልተኛ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት የመዘርጋት፣
2) ከምርጫው በፊት ምርጫው ሊመራበት የሚችል ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል የሚችል የሕገመንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን አቋቁሞ ሥራ ማስጀመር፣
3) ትክክለኛ የሆነ የሕዝብ ውክልና እንዲኖር የሕዝብ ቆጠራ ማካሄድ፤
4) በዐማራውና በሌሎች ነገዶች ላይ የተፈጸመውን የዘር ጥቃት፣ ማፈናቀልና ማሳደድ አጣርቶ ለፍትሕ የሚያቀርብ ገለልተኛ ኮሚሽን ማቋቋም፤
5) ብሔራዊ መግባባትና አንድነትን ለመመለስ እንዲቻል የተቋቋመው ኮሚቴ ተጠናክሮ ከምርጫው በፊት ብሔራዊ ዕርቅና መግባት እንዲፈጠር ማድረግ፣ የሚሉት በተግባር እንዲገለጹ አበክረን እንጠይቃለኝ። እውን እንዲሆኑም የበኩላችን ያላሰለሰ ጥረት እናደርጋለን!

እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስም ገዥው ፓርቲ ብቻዬን ወይም እኔ ባልኩት ይሂድ ካለ የተጨመረለት ጊዜ የአምባገነነት ማጠናከሪያ እና የባከነ ጊዜ ከመሆን አያልፍም። የተቃዋሚዎች የተሳትፎ ጥያቄም አግባብነት ኖሮት ጎልቶ የሚወጣው እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚኖራቸው ተሳትፎ መጎልበት እንደሆነ ዐኅኢአድ ያምናል።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆ መዝለቅ ዋስትና ነው!

የትግላችን ግብ ሕዝቡን የሥልጣኑ ባለቤት ማድረግ ነው!

የሕገ-መንግሥቱ መሻሻል የኢትዮጵያ አንድነት መቀጠል አስተማማኝ ነው!